የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ)

የጤና ፖሊሲ መነሻ ሰነድ

(የመጨረሻ ረቂቅ)

መስከረም ***2013***

ማውጫ

የጤና ፖሊሲ ረቂቅ ሰነድ 3

ምዕራፍ አንድ 3

ምዕራፍ ሁለት 3

የጤና ፖሊሲው መርሆች 3

ምዕራፍ ሶስት 3

የጤናዉ ፖሊሲ ግብና አቅጣጫዎች 3

ምዕራፍ አራት 4

የተቀናጀ የጤና አስተዳደር (Shared Health Governance) 4

ምዕራፍ አምስት 5

የጤና አገልግሎት 5

ምዕራፍ - ስድስት 8

የፈውስ ጤና አገልግሎት 8

ምዕራፍ ሰባት 12

የጤናው ዘርፍ የሰዉ ኃይል ልማት 12

ምዕራፍ ስምንት 16

የመድሀኒት እና የህክምና ግብአት አቅርቦት 16

ምዕራፍ ዘጠኝ 17

የጤና አገልግሎቶች አሰጣጥ 17

ምዕራፍ አስር 19

የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት 19

ምዕራፍ አስራ አንድ 22

የጤና አገልግሎት የሃብት ምንጭና አስተዳደር 22

የጤና ፖሊሲ ረቂቅ ሰነድ

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

የጤናን ፖሊሲ አቅጣጫዎች ለማስቀመጥ ጤናን ምሉዕ በሆነ መልኩ መተርጎም አስፈላጊ ነው፤ ከጤና አገልግሎት አንጻር ብቻ በተቃኘ ፖሊሲ ላይ ተመርኩዞ ዜጎችን ጤናማ እና አምራች ማድረግ አይቻልም። ጤና ብለን ግብርናን ካላካተትን ከምግብ አቅርቦት እና ተደራሽነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ልንፈታ አንችልም ፣ ከንጹህ ውሃ አቅርቦት ጋር አያይዘን ሳንስራ ውሃ ወለድ በሽታዎችን መከላከልም ሆነ መፈወስ የሚቻል አይደለም ፣ ከአካባቢያዊ ጥበቃና ከአየር ንብረት ለውጥ ፣ ከሰብዓዊ መብት ፣ ከትምህርት ፣ ከባህል እና ህዝባዊ ግንኙነት ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጋር በተቀናጀ መልኩ ካልተሰራ ዜጎችን ጤናማ እና ምርታማ ማድረግ የማይታሰብ ነው። ይህን እውን ለማድረግ እንዲረዳን የተቀናጀ የጤና አስተዳደርን የጤና ፖሊሲያችን ዋና ክፍልና የማህበረሰቡን የጤና ፍላጎትና ምኞት እዉን ለማድረግ አይነተኛ አቅጣጫችን አድርገን እንሰራለን።

ምዕራፍ ሁለት

የጤና ፖሊሲው መርሆች

- ጤናን ማህበረሰባዊ ፍትህን ከማስፈን አንጻር በማየት ለሁሉም ዜጋ ቤተሰብና ማህበረሰብ ጤናማ የመሆንን መብት ለማረጋገጥ መትጋት።
- ዜጎች ከጤና ጋር በተያያዘ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲጨምር ልዩ ትኩረት በመስጠት፤ በጤናው መዋቅር ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ማረጋገጥ፤ ብሎም በፖለቲካ ስልጣን አደረጃጀት፣ የሃብት ክፍፍልና በማህበራዊ አገልግሎቶች ፍትሃዊ የሆነ ክፍፍልን በማረጋገጥ ጤናማ፣ የተረጋጋ፣ ዉጤታማና አምራች ግለሰብና ማህበረሰብን ለመፍጠር መስራት።
- ለጋራ ዉጤታማነትና ተጠቃሚነት የዜጎች (ግለሰብ፣ ቡድን፣ ማህበረሰብና ድርጅቶች) ትብብርን እዉን በማድረግ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ፍትሃዊነትን በተደላደለ መሰረት ላይ መገንባት።

ምዕራፍ ሶስት

የጤናው ፖሊሲ ግብና አቅጣጫዎች

የጤና ፖሊሲው ግብ

- በዜጎች ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ የመንግስት ድጋፍና ክትትል ያልተለየው የተቀናጀ የጤና አስተዳደር ያለው መዋቅር በመገንባት ጤናማ እና በራሱ የሚተማመን አምራች ዜጋ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ ማፍራት።

የጤና ፖሊሲዉ አቅጣጫዎች

- ለጤናዉ ዘርፍ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ በሆኑት መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተቀናጀ አስተዳደር በመመስረት ጤናማ፣ ዉጤታማና ምርታማ ዜጋን፣ ቤተሰብንና ማህበረሰብን ለመፍጠር በጋራ ተግባራዊ የሚያደርጉት ግብ አዉን ማድረግ።
- ፍትሃዊ በሆነ መልኩ የፈዉስና (Curative Health care) የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶችን (Promotive and Preventive Health Care) ስርጭት በሁሉም ሃገሪቱ ክፍል ማረጋገጥ።
- ጥራቱን የጠበቀ የጤና ትምህርት፣ የመከላከል፣ የፈዉስ፣ የክትትል ህክምናና የማገገም ጤና አገልግሎት ሁሉም የሃገሪቱ ዜጋ ምንም ልዩነት ሳይፈጠር የሳይንስና ቶክኖሎጂ እድገት በደረሰበት ልክ በሁሉም የሃገሪቱ የቆዳ ስፋት ለማዳረስ መትጋት።
- በመንግሰት፣ በግሉ ማህበረሰብ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ከውጭ በሚገኝ አርዳታ፣ አለም አቀፋዊ ብድርና በማህበረሰብ ጥምረትና ትብብር የማህበረሰብ ጤና ዋስትና ስርአት በመዘርጋት በጤና አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች የቀጥታ ጥሬ ገንዘብ ክፍያ (Out of Pocket) መጠንን መቀነስ።

ምዕራፍ አራት

የተቀናጀ የጤና አስተዳደር (Shared Health Governance)

ጤና እና የጤና አገልግሎት ተመሳሳይ የሚመስሉ ግን በጣም የተለያዩ መሰረታዊ አስተሳሰቦች ያሏቸው ሁለት ፅነሰ ሃሳቦች ናቸዉ። የሁለቱን ፅንሰ ሃሳቦች ልዩነታቸዉን በሚገባ ለይቶ በማዎቅ፣ በመረዳትና ተግባራዊ በማድረግ የዜጎች፣ የቤተሰብና ማህበረሰባዊ ጤንነትን በማረጋገጥና ጤናማ፣ ንቁ፣ ሀገሩንና አራሱን የሚያከብር አምራች ዜጋ መፍጠር ይቻላል። ምንም እንኳን የጤና አገልግሎት የግለሰብና ማህበረሰብ ጤና ንኡስ ክፍል ቢሆንም የተለያዩ ጥናቶች እነደሚያሳት የዜጎችና የማህበረሰብ ጤናን በማረጋገጥ ረገድ የሚጫወተዉ ሚና **10**% የበለጠ አይደለም። በዚህ መሰረት ዘጠና በመቶ የሚሆነዉን ግዙፍ የጤና ክፍል ተፅዕኖ የሚፈጥሩት ማህበራዊ ሁኔታዎች **15**%= የዘረመል ውርስ **30**% = ከባህሪ ጋር የተወራረሱ **40**% አና በከባቢያዊ ሁኔታ ተፅእኖ ምክንያት **5**% ናቸው። ከላይ የተዘረዘሩት ጤናን ለመጠበቅ ወይንም ለማወክ አቅም ያላቸዉ መሰረታዊ ምክንያቶች በትኩረት ስንመለከት የግለሰብ ወይንም የማህበረሰብን ጤና ለማስተካከል የጤና አገልግሎትን ማረጋገጥ ብቻውን በቂ እነዳልሆነ ያስገነዝባል። የግለሰብንም ሆነ የማህበረሰብን ጤና ለማረጋገጥ በጤና አገልግሎቱ፣ በማህበራዊ ዘርፉ፣ በዘረመል ምርምሩ ዘርፍ፣ በስነአእምሮው ዘርፍ እና የተፈጥሮ ሚዛንን በመጠበቅ የጋራ ትብብርና የተቀናጀ እንቅስቃሴንና ለጤናማ ዜጋ የጋራ መድረክን መፍጠርን የሚጠይቅና ግድ የሚል ጉዳይ ነው።

ምዕራፍ አምስት

የጤና አገልግሎት

ሁሉን አቀፍ ለሰዉ ልጆች የጤና መብት ድንጋጌ (Universal Declaration for Health Right (UDHR) አነቀፅ **25** ሁሉም ስው ከነቤተሰቡ ደረጃዉን በጠበቀ ጤናና በተሙዋላ ደህንነት የመኖር መብት አለዉ። ይህም ምግብን፣ አልባሳትን፣መጠለያን፣ የጤና አገልግሎትና የተሟላ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ያካትታል። ከዚህ በተጨማሪ ከመደበኛ ስራ መገለል ሲያጋጥም፣ በህመም ጊዜ፣ አካል ጉዳተኛነት ሲያጋጥም፣ የትዳር አጋር በሞት ሲለይ፣ በጡረታ እድሜ ክልል እና ሌሎች ህይወትን አዳጋች የሚያደርጉ ከቁጥጥር ውጪ የሆኑ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ አስተማማኝ የህይወት ዋስትና ማረጋገጥን ያካትታል።

ከላይ የተገለፀዉ ድንጋጌ በዘረዘረዉ መጠን ለዜጎች ጤናቸውን እውን ለማድረግና የዜጎችን፣ ቤተሰብና የማህበረሰብን የጤና ፍላጎቶችንና ምኞቶችን በተሟላ መልኩ ለማሳካት የአንድ አገር የጤና አገልግሎት መዋቅር የዜጎችን፣ የቤተሰብንና የህብረተሰብን የጤና ደረጃ ማሻሻል ይኖርበታል፤ ማህበረሰቡን ለህመም የሚዳርጉ መንስኤዎች ለመከላከል ብቁ መሆን አለበት፤ በህክምና ምክንያት ማህበረሰቡ አላስፈላጊ ለሆኑ ወጪዎች አንዳይዳረግ መከላከል ይኖርበታል፤ ፍትሃዊ የሆነ ሰዎች ተኮር አገለግሎቶችን እውን ማድረግ እና የማህበረሰቡ አባላት ህይወታቸዉንና ኑሮአቸውን በሚመለከት ጉዳዮች ሁሉ ሙሉ ተሳትፎ የማድረግ መብታቸውን ማክበር አለበት። በኢትጵያ የጤናው ዘርፍ ግዴታዎቹን በአግባቡ እንዲወጣ ለማስቻል ኢዜማ የጤና አገልግሎት ዘርፉን የፈዉስ ጤና አገልግሎቶች (Curative Health care)ና የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች (Promotive and preventive Health Care) በማለት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች በመክፈል ወደተግባር ይገባል።

ላለፉት አመታት የኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ የጤና ችግሮችን ለመፍታት የጤና አገልግሎት ዘርፉን ብቻ ተግባራዊ በማድረግና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተናጥል ጥረት እወጣዋለሁ ከሚል ከተሳሳተ ሃሳብ ከመነሳቱ በላይ የፈዉስ ጤና አገልግሎቱን(Curative Health care) ሙሉ በሙሉ ከእይታዉ አድማስ በማውጣት በማህበረሰብ ጤና አገልግሎቱ (Promotive and preventive Health Care) ብቻ የሀገሪቱን ግዙፍ የጤና ችግር አወጣዋለሁ በማለቱ ልንወጣዉ ከማንችለው የጤና ችግሮች አዙሪት ውሰጥ ገብተናል።

5.1 የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት (Promotive and preventive Health Care)

መንግስት የማህበረሰብ ጤና አገልግለትን (**ሓቄቂቂቂቋሻባስ ሮቃሳ ቅቄስባስቃቋሻባስ ሃስሮቂቋሻ ኑሮቄስ**) ለማህበረሰቡ ለማዳረስና ተግባራዊ ለማድረግ በሚል እሳቤ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም የተመደበለት ሃብት ውስንነትና ዘላቂ ባለመሆኑ፤ በአገልግሎት ሂደቶቹ ውስጥ የክንውኖችን ውጤቶች ለመከታተልና ለመቆጣጠር ትክክለኛ ዘዴዎችና መመሪያዎች ባለመኖራቸው፤ የሰለጠነና በስነምግባር የታነፀ የሰው ሃይል እጥረት በመኖሩና የሃገሪቱ ፖለቲከኞች ቁርጠኝነት በመጥፋቱ የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቱ መድረስ የሚገባዉ ደረጃ ላይ ሳይደርስ ቀርቷል። የማህበረሰብ አቀፍ ጤና አገልግሎት ከማህበራዊ ከሰብአዊ መብቶች፣ ፍትሀዊነትና እና እኩልነት ጋር ጥብቅ ቁርኝት መኖሩ አሌ አይባልም። የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት በአግባቡ ከተተገበረ በረዥም ጊዜ የጤና አገልገሎት ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚቀንስና አዋጪ በመሆኑ ኢዜማ ከፍተኛ ትኩረት ሠጥቶ የሚሰራበት ይሆናል። ኢዜማ እነዚህን ድክመቶች በመመልከትና የወደፊት ሂደቱን ለማስተካከል ሁሉም የማህበረሰብ ጤና ትግበራ በአዳዲስ ፈጠራና ጥናትን መሰረት ባደረገ መረጃ ላይ መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ይደርጋል።

በከፍተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸዉን የጤና ችግሮች በመለየትና በመረጃ ላይ በመመስረት ጥቅል መፍተሄዎችን (Package) ማዘጋጀት፤ ወቅታዊና ዉጤታማ የሆነ የትግበራ መከታተያ መገምገሚያና የፕሮገራም ማሻሻያ አሰተዳደራዊ መንገዶች ይቀይሳል፤ በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በግል ባለሃብትና በማህበረሰቡ መካከል የትብብርና አጋርነትን በመመስረት እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤ በማህበረሰብአዊ ጤና አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች፤ በመንግስት (ዉሳኔ ሰጭዎች)ና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ መካከል ትክክለኛና ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ዝውውር እውን ያደርጋል፤ መንግስት ሃብት በማሰባሰብና በማንኛውም የጤና ትግበራ ላይ ድጋፍ ለማድረግና ለማስተባበር ቁርጠኛ ይሆናል።

5.1.1 የማህበረሰብ ጤና ማዕከላት

በአጠቃላይ በማህበረሰብ ጤና ማዕከላት የሚሰጡት የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች ጥልቅ ጥናት፣ ምርምርና ቅደም ተከተል ማውጣት ቢያስፈልግም ለመነሻ ያህል የሚከተሉት የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች በማዕከሎቹ ይሰጣሉ። እነሱም የጤና ማበልጸግ ፤ በሽታን መከላከል፤ መሰረታዊ የህክምና አገልግሎት፤ የማገገም (Rehabilitation) እና የማስታገስ (Palliative care) አገልግሎቶች ይሆናሉ። የማህበረሰብ ጤና ማዕከሎች ለራሳቸውና ለመሰረታዊ ጤና ማዕካላት ለሚሰጧቸዉ አገልግሎቶች ስልቶችን (Strategy)፣ መመሪያዎችን (Guideline)፣ እቅድ ማውጫ (Planning Format)፣ መተግበሪያ (Implementation) እና መረጃ ማቀበያዎችን (Reporting format) ያዘጋጃሉ ተግባራዊነቱንም ይከታተላሉ።

5.1.2 የጤና ማጎልበት (ማበልፀግ)

በማህበረሰብ ጤና ማዕከሎች በእናቶች እና ህጻናት ጤና ማሻሻል፣ በስነምግብ፣ በባህሪ ለውጥ ትምህርት፣ በቤተሰብ ምጣኔ፣ በስነተዋልዶ ጤና፣ በንፁህ ዉሃ አቅርቦት፣ በግል እና በአካባቢ ንጽህናን በማህበረሰቡ ውስጥ ያረጋግጣል።

5.1.3 በሽታን መከላከል

በማህበረሰብ ጤና ማዕከሎች ባለፉት አመታት ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል የተተገበሩ ስልቶችን ማጠናከር፤ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ልዩ ልዩ አቀጣጫዎችንና ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ፤ ወረርሽኝ መከላከል እና መቆጣጠር ላይ ከፍተኛ ትኩረት እና ክትተል ማድረግ። ድንገተኛ አደጋ በተለይም የትራፊክ አደጋን መከላከልና መቆጣጠር ላይ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ።

5.1.4 መሰረታዊ ህክምና አገልግሎት

ለእናቶችና ህጻናት ህክምና (ቅድመ ወሊድ ክትትል፤ የማዋለድ (ላልተስተካከለና አጣዳፊ ውሳኔ ለሚያስፈልጋቸዉ ማዋለድን ያካተተ) አገልግሎት፤ ድህረ ወሊድ ክትትል ለህፃናት የክትባት፣ የጤናና እድገት ክትትል፣ ወዘተ*.*) አገልግሎቶችን መስጠት፤ ለመሰረታዊ ህክምና አገልግሎት የጥራት ደረጃ እና መመሪያ ማዘጋጀት፤ የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎትን መስጠት፣ የአገልግሎቱን ተደራሽነት እና ጥራት ማሻሻል፤ የቱበርክሎሲስ፣ የስጋ ደዌ እና የሀሩር በሽታ ሕክምና መስጠትና የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ቅኝቶችን ማድረግ፣ መቆጣጠር እና የጉዳት መጠናቸውን መቀነስ፤ የወባ እና ኤች አይ ቪ ላይ የተገኙ ስኬቶቸን ማስቀጠል።

5.1.5 የማገገም (Rehabilitation) ጤና አገልግሎት

ባለፉት አመታት የማገገማ እንክብካቤ በዋነኛነት በከፍተኛ የህክምና እርከን ላይ በጣም በተጨናነቀ ሁኔታ ሲሰጥ መቆየቱ ይታወቃል። ይህን ችግር ለመቅረፍ አገልግሎቱን ህብረተሰቡ በቅርብ በመሰረታዊ የጤና ማዕከላት እንዲያገኝ ማድረግ።

5.1.6 የማስታገሻ ጤና አገልግሎት (Palliative Care)

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ባለፉት ግዜያት ትኩረት የተነፈጋቸዉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች የዜጎችን፣ ቤተሰብ እና ማህበረሰብ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት እየጨመረ መጥቷል (የቅርብ ግዜ ጥናት ***52%*** መሆኑን ያሳያል)። አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ካልተወሰደ ስርጭታቸውና ጉዳታቸዉ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚጨምር ይጠበቃል። ይህን መሰረት በማድረግ የማስታገስ ጤና አገልግሎቶች የማህበረሰብ ጤና ማዕከላት ውስጥ ተካተዉ እንዲሰጡ ይደረጋል።

5.1.7 ማኅበረሰብን በጤና አገልግሎቱ ማሳተፍ

ህብረተሰቡ በእናቶችና ሕፃናት፣ በወጣቶች፣ በአካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን፣ ወዘተ.. ቡድኖች ራሱን በማደራጀት፣ ማህበረሰብ መር ውይይቶች እንዲጎለብቱ በማድረግ፤ ዜጎች ቤተሰቦችና ቡድኖች በህይወት የመኖር መብቶቻቸውን ለማረጋገጥ፤ ጤና ነክ ፍላጎታቸውና ምኞታቸዉን እንዲጠይቁና ለተግባራዊነቱም የበኩላቸዉን ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማብቃት፤ በማህበረሰብ ጤና ማዕከላት የሚሰጡት የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶችን በተመለከተ ለማህበረሰቡ ማስተዋወቅ፣ አገልግሎቶቹን በአግባቡ አንዲጠቀሙ በማድረግ፣ ወደማዕከላቸው የሚመጡትን ተጠቃሚዎች በአቅማቸውና በተሰጣቸዉ ኃላፊነቶች ልክ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና በመስጠት እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ማህበረሰብ ጤና ማዕከላት ማስተላለፍ።

5.1.8 የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት አወቃቀር

የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቱ በማህበረሰብ ጤና ማዕከላትና (Health Centers) በመሰረታዊ ጤና ማዕከላት (Basic Health Unit) ውስጥ የሚሰጥ ይሆናል። ኢዜማ በሚያደራጀው የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ አንድ የማህበረሰብ ጤና ማዕከል እያንዳንዳቸዉ ለ***5000*** ስዎች አገልግሎት የሚሰጡ አምስት መሰረታዊ ጤና ማዕከሎችን በማደራጀት በዙሪያዉ ለሚኖሩ ከ***25000*** እስከ ***30000*** ሰዎች አገልግሎት ይሰጣሉ።



የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት አወቃቀር

5.1.9 የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት የሰዉ ኃይል አደረጃጀት

መሰረታዊ ጤና ማዕከሎች በማህበረሰብ ጤና አገልግሎት ላይ በበቂ ሁኔታ ስልጠና ያገኙ፣ እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውን፣ ግብረገባቸውንና ስነምግባራቸውን ያስመሰከሩ አንድ ጤና መኮንን ፣ ሁለት የማህበረሰብ ነርሶችና ሁለት ጤና ተጠሪዎች ተመድበው ማህበረሰብን የማብቃትና የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቱን ከማህበረሰብ ቡድኖች ጋር በመተጋገዝና በመደጋገፍ ተግባራዊ ያደርጋሉ።

ማህበረሰባዊ ጤና ማዕከሎች እንደሚያገለግሉት የህዝብ ብዛት ብዛታቸዉ የሚወሰን ሆኖ ጠቅላላ ሀኪሞች፣ ጤና መኮንኖች፣ አዋላጅ ነርሶች፣ ጠቅላላ ነርሶች፣ ላቦራቶሪ ቴክኒሻኖች፣ የመረጃ አስተዳደር ሰራተኞች፣ ወዘተ.ይ ይመደባሉ፡ ፡ ከዚህ በተጨማሪ ጤና ማዕከሎቹ የተሟላ የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞች ይመደቡላቸዋል። ይህም አደረጃጀት ከተቀናጀ የጤና አስተዳደር መዋቅር ጋር ተናብቦ የሚደራጅ ይሆናል።

በማህበረሰብም ሆን በመሰረታዊ የጤና ማዕከላት ተመድበው የሚሰሩት ባለሙያዎች በቦታቸዉ ላይ የሚመደቡት ፍፁም ከፖለቲካ ነፃ በሆነ መልኩ በዜግነታቸውና በሚኖራቸው እውቀት፣ ክህሎትና ስነምግባር ብቻ ተመርጠው ሲሆን የማዕከሎቹ አስተዳደራዊ መዋቅርም እንደዚሁ ከፖለቲካ ተፅዕኖ የፀዳ ይሆናል።

ምዕራፍ - ስድስት

የፈውስ ጤና አገልግሎት

ዘመኑ የደረሰበትን የፈውስ አገልግሎት በህብረተሰቡ ፤ በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በግል ባለሀብቶች ትብብር በአግባቡና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለማዳረስ በመቀናጀትና በመተባበር ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የጤና አመራር በሌለበት ፈውስ ሰጪ የጤና አገልግሎቶች ሚዛናቸውን በጠበቀ መልኩ ሙሉ ለሙሉ ለጠቅላላው ለማህበረሰቡ ለማዳረስ እንደሚያዳግት ኢዜማ ጠንቅቆ ይረዳል።

ከዚህ መሰረታዊ ሃሳብ በመነሳት ኢዜማ የፈውስ ጤና አገልግሎቱን የሃገሪቱ የፖለቲካ፣ ማህበራዊ ሁኔታና ምጣኔ ሃብታዊ አቅም በሚፈቅደው መጠን፣ የማህበረሰቡን ፍላጎት ለማሙዋላትና ምኞታቸውን ለማሳካት ዓላማው ባደረገ መልኩ ተደራሽና ፍትሃዊ ለማድረግ ይሰራል። እነዚህን ዓላማዎች እውን ለማድረግ በጤና አመራርና አስተዳድር፣ በጤና መረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም፣ ሃብት አሰባሰብና አስተዳደርን ባካተተ መልኩ በሃገሪቱ ያለፈ ታሪክ፣ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ እና መጪውን የሃገሪቱን ሁኔታዎች ባካተተ መልኩ ፖሊሲ ነድፎ በስራ ለመተርጎም ተዘጋጅቶዋል። እነዚህን አውነታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ኢዜማ በቀረፀዉ ሁሉን አካታች በሆነዉ የጤና ፖሊሲ ማካኝነት ጠንካራ የጤና አመራርን በመፍጠር ፈውስ ሰጪ የጤና አገልግሎቶች ሚዘናቸውን፣ ጥራታቸውንና ፍትሃዊነታቸውን በጠበቀ መልኩ በኢትዮጵያ ውስጥ እውን መሆናቸውን ያረጋግጣል።

የጤና አግልግሎቶቹ ሚዘናቸውን፣ ጥራታቸውንና ፍትሃዊነታቸውን በጠበቀ መልኩ እውን ለማድረግ አስፈላጊ የሆነውን ሃብት ከባለሀብቱ፣ ከመንግስት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከማህበረሰቡ በማሰባሰብ፣ በማቀናጀትና በማስተባበር ሀገራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ፈውስ ሰጪ ጤና አገልግሎቶችን ትክክለኛ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ጠንካራ የትግበራ መመሪያዎችና እያንዳንዱን የፈውስ ሰጪ ጤና አገልግሎት ክፍሎች ባናበበ መልኩ የሃብት ስርጭትን የግድ ይላል።

የፈውስ ጤና አገልግሎቶቹ ሚዘናቸውን፣ ጥራታቸውንና ፍትሃዊነታቸውን በጠበቀ መልኩ እውን ለማድረግ ወሳኝና መሰረታዊ የሆኑት ግበአቶቹ የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- ጠንካራ፣ ችግር ፈቺና ራእይ ያለዉ የጤና አመራርና አስተዳደር፤
- የጤናዉ ዘርፍ ተግዳሮቶችን፣ የጤና አገልግሎቶቹ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ነባራዊ ሁኔታዎችንና የጤና ዘርፍ ክንዉኖችን ባካተተ መልኩ የመረጃ አሰባብ፤
- ምርምር ማድረግ፣ የምርምር ዉጤቶችን ስርጭትና አጠቃቀም ስርአትን እዉን ማድረግ፤
- የፈዉስ ሰጪ ጤና አገልግሎቶችን በዘመነና በተሻሻለ መልኩ ለመተግበርና ኢፍትሃዊነትን ለመቀነስ/ለማሰወገድ በቂና አስተማማኝ የሃብት ምንጭን ማረጋገጥ፤
- በእዉቀቱ የዳበረ፣ ክህሎቱ ከፍተኛ የሆነ፣ በስነምግባር ታነፀና የአስተሳሰብ ልዕልናዉ ከፍተኛ የሆን የሰዉ ኃይል ማፍራት፤
- አስፈላጊና ፈዋሽ መድሃኒቶችንና የቴክኖሎጂ ዉጤቶችን ተደራሽ ማድረግ፤

ባጠቃላይ፤ የፈዉስ ጤና አገልግሎት አጠቃቀም፣ የሰዉ ኃይል አስተዳደር፣ የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች አስተዳደርና የፈዉስ ሀክምና አሰጣጥ ላይ ደረጃቸዉን የጠበቁ ስልቶችን፣ ስልታዊ ዕቅዶችን፣ መመሪዎችንና ዝርዝር የስራ ዕቅዶችን ቀርፆ ወደተግባር ይገባል፡፡

6.1 በየእርከኑ የሚካተቱት የፈዉስ ህክምና ፕሮግራሞች

በወረዳ ሆስፒታሎች አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ የህክምና ፈላጊዎች ለህክምና አገልግሎት ወደ ሆሰፒታሎች በሚሄዱበት ወቅት አሁን እነደተለመደዉ ለመጡበት የጤና ችግር የሚያሰፈልጋቸዉን የጤና አገልግሎቶች ብቻ በመስጠት ስለሚሸኙ ሰዎች ባንድ ላይ ተሰባስበዉ በመገኝታቸዉ በጤና ድርጅቶቹ ዉስጥ ስለሚሰጡት አጠቃላይ የጤና አገልግሎቶች የማስተዋወቅና የማስተማር (Health Promotion) እንዲሁም በሽታን ስለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ መልዕክቶችን ማስተላለፍ ሲቻል አጋጣሚዎች አንደሚባክኑ የተለያዩ ጥናቶች (Netsanet Fetene Wendimagegn እና Marthie C Bezuidenhout) ያሳያሉ፡፡ የፈዉስ ህክምና የሚጠይቀዉ ክፍያ ከፍተኛ በመሆኑና ስለተለያዩ የህክምና አገልግሎቶች ማሳወቅና ስለበሽታዎች መንስኤና ስለመከላከያ ዘዴዎች የማስገንዘብ አጋጣሚዎችን በማባከናችን ምክንያት ማህበረሰቡን ለተለያ በሽታዎች ከመዳረጉ በላይ አላስፈላጊ ላልሆነና ለተጋነነ ወጭ ይደረጋል፡፡

ኢዜማ ከላይ የተጠቀሱትን የጥናትና ምርምር ግኝቶችን ግምት ዉስጥ በማስገባት ከማህበረሰብና መሰረታዊ የጤና ማዕከሎች ቀጥሎ ለህብረተሰቡ በቅርበት በሚገኙት የወረዳ ሆስፒታሎች ዉስጥ ስለጤና አገልግሎቶች ማሳወቅና ስለበሽታ መንስኤዎችና መከላከያ ዘዴዎች ከፈዉስ ህክምናዉ ጋር በተጠናከረ መልኩ መሰጠት አንዳለበት በፅኑ ያምናል፡፡

6.1.1 ማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች በወረዳ ሆስፒታሎች

- ወደ ወረዳ ሆሰፒታሎች ለተለያ ጤና አገልግሎት ለሚመጡት ታማሚዎችና ተንከባካቢዎቻቸዉ በጤና ድርጅቶች ስለሚሰጡት የጤና አገልግሎቶች በዝርዝር የማስተዋወቅና (Health Promotion) በማህበረሰቡ ዉስጥ በሰፊው የጤና እንከኖች ስለሆኑት በሽታዎች መንስኤዎቻቸውንና የተለያዩ የመከላከል ዘዴዎችን (Disease Prevention) የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም መልዕክቶችን ማስተላለፍ፡

- በሆስፒታሎቹ ዉስጥ ከሚሰጡት የጤና አገልግሎቶች በዝርዝር የማስተዋወቅና (Health Promotion) እና ስለበሽታዎች መንስኤዎቻቸዉንና የተለያዩ የመከላከል ዘዴዎችን (Disease Prevention) ግንዛቤ ከማስጨበጥ በተጨማሪ ወረዳ ሆስፒታሎች በማህበረሰብና መሰረታዊ የጤና ማዕከላት ዉስት ለሚሰሩት ለተለያዩ የዘርፍ ባለሞያዎች በሚሰጡት የጤና አገልግሎቶች ላይ ተከታታይ ስልጠናዎችን፣ ቁዋሚ ዉይቶችን ማከሄድ እና በተለያዩ ዘርፎች ጥናታዊ ምርምር በማድረግ የሚገኙትን ዉጤቶች ለአገልግሎቶቹ ማሻሻያ እንዲዉሉ ማድረግ በስራ ዝርዝሮቻቸዉ ዉስጥ የካተታል

6.1.2 የፈዉስ ጤና አገልግሎቶች በወረዳ ሆስፒታሎች

የፈውስ ጤና አገልግሎት ታማሚዎች ከተጠናወታቸዉ ህመም መሻሻል፣ የበሽታ ምልክቶችን (ስቃይ ስሜቶችን) ለማጥፋት ብሎም ሙሉ ለሙሉ ከተጠናወታቸዉ ደወየ ነፃ እነዲሆኑ የሚረዳ ህክምናና ክትትል ነዉ። የፈዉስ ጤና አገልግሎት መሰረታዊ ዓላማዉ ለህሙማን ከበሽታቸዉ ነፃ ለማድረግና ህመማቸዉን ተከትሎ የሚመጣን ተጉዋዳኝ ህመሞችን ለመቀነስ ሲሆን በማህበረሰብ ደረጃ ደግሞ በሚከሰቱ ህመሞች ምክንያት የሚከሰተዉን የሞት መጠን ለመቀነስ ነው።

በወረዳ ሆስፒታሎች የያንዳንዱን ዜጋ የአካል እና የአእምሮ ጤንነትን ለማረጋገጥ ሊረዱ የሚችሉ የፈዉስ አገልግሎት ፕሮግራሞች የሚከተሉት ናቸዉ።

- በአንድ መልከአ ምድራዊ አካባቢ የፈዉስ ጤና አገልግሎት ለመስጠት ከመጀመሩ በፊት ያካባቢዉን ተፈጥሮ (መልከአምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ፀባይ (ቆላ፣ ወይና ድጋና ደጋ)፣ የዕፀዋት ዓይነትና ስርጭት፣ ዋናዋና የበሽታ ዓይነቶች ለበሽታዎቹ የተጋለጡ ማህበረሰቦችንና በበሽታዎቹ ለመያዝ የሚያሰጋቸዉን በዝርዝር ማጥናት ተቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት።
- በዝርዝር ጥናቱ የተለዩት በሽታዎች ቅደምተከተል ከወጣላቸዉ በሁዋላ አስፈላጊ (Essential Druge) የመድሃኒት ዝርዝር፣ ለየበሽታዎቹ የህክምና መመሪያዎች፣ የጤና ባለሞያ አይነቶችና (የስልጠና አይነቶች) ብዛት እንዲሁም የጤና አገልግሎቱ አስተዳደራዊ መዋቅር ይወሰናል፡

    1. የውስጥ ደዌ ህክምና
    2. የሕጻናት ህክምና
    3. የቀዶ ህክምና
    4. የማህጸን ጽንስ ሕክምና

የወረዳ ሆስፒታሎች ከ ***40—50*** የህክምና አልጋ ይኖራቸዋል፤ ከያንዳንዳቸዉ (የዉሰጥ ደወዬ፣ ቀዶ ህክምና፣ የህጻናትና የማህፀንና ጽንስ) ሀኪሞች እንዲኖራቸው ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪ የማኅበረሰብጤና ተመራማሪዎች፣ የጤና መረጃ አስተዳደር ባለሞያዎች፣ ነርሶች፤ የማህበራዊ (ስነልቦና) አገልግሎት ሰራተኞች፤ የስነ ምግብ እና ሌሎችም መካከለኛ ስልጠና የወሰዱ ባለሙያዎችን አካቶ እንዲደራጅ ይሆናል።ከማህበረሰብ አቀፍ ጤና አገልግሎት ጋር በአንድ ላይ በወረዳ የተቀናጀ የጤና አስተዳደር ድጋፍ እና ክትትል ይደረግለታል።

6.2 የፌደራል ሆሰፒታሎች

በፌደራል አስተዳደሮች ዉስጥ በሚገኙ ወረዳዎች የፈዉስ ጤና አገልግሎት ለመስጠት ከመጀመሩ በፊት የአካባቢዉን ተፈጥሮ (መልከአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ፀባይ (ቆላ፣ ወይና ድጋና ደጋ) ፣ የዕፀዋት ዓይነትና ስርጭት፣ ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች ለበሽታዎቹ የተጋለጡ ማህበረሰቦችንና በበሽታዎቹ ለመያዝ የሚያሰጋቸውን ማህበረሰቦች በዝርዝር ለማጥናት አስፈላጊውን ዕገዛ ማድረግ ዋነኛ ተግባራቸው መሆን አለበት። በዝርዝር

ጥናቱ የተለዩት በሽታዎች በፌደራል አስተዳደር ደረጃ ቅደም ተከተል ከወጣላቸው በሁዋላ አስፈላጊ (Essential Druge) የመድሃኒት ዝርዝር፣ ለየበሽታዎቹ የህክምና መመሪያዎች፣ የጤና ባለሙያ አይነቶችና (የስልጠና አይነቶች) ብዛት እንዲሁም የጤና አገልግሎቱ የምርምር፣ መረጃ አያየዝና አስተዳደራዊ መዋቅር ይወሰናል።

6.2.1 የፌደራል ሆስፒታሎች የሰዉ ኃይል አደረጃጀት

የፌደራል ሆስፒታሎች በፌደራል ደረጃ የሚደራጁ ሆነዉ በፌደራል የተቀናጀ የጤና አስተዳደር ከፍተኛ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። አያንዳንዳቸው ከ*300 –1000* የህክምና አልጋ ሲኖራቸው በሁሉም የህክምና መስክ ሰፕሺያሊሰቶችና ንዑስ ስፔሺያሊሰቶች ይመደቡላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ የጤና ተመራማሪዎች፣ የመረጃ አያያዝ ባለሞያዎች፣ ሌሎች አጋዥ ባለሙያዎችና አስተዳደራዊ ሰራተኞች ይኖሩዋቸዋል።



የጤና አገልግሎ ዘርፉ አደረጃጀትና አወቃቀር

6.3 ልዩ ሆሰፒታሎች (Tertiary Care Centers)

ልዩ ሆሰፒታሎች በዋናነት ከፍተኛ የሆነ የኑዋሪዎች ቁጥር ባላቸዉ ትልልቅ ከተሞች ውስጥ የሚደራጁ ይሆናሉ። እያንዳንዳቸው

- እስፔሻሊሰት እና ንዑስ ስፔሻሊስት ሃኪሞች ይኖሩዋቸዋል፤ ከዚህ በተጨማሪ በሚኖሩት እስፔሻሊሰት ሃኪሞች ተመጣጣኝ የሆኑ ሌሎች ባለሞያዎች ይኖሩዋቸዋል። እያነዳንዳቸዉ ከ*1000* በላይ የህክምና አልጋዎች የሚኖሩዋቸው ይሆናሉ።
- ከህክምና አገልግሎቱ በተጨማሪ ትልቅ የህክምና ጥናትና ምርምር ማዕከል በመሆን እንዲያገለግሉ ሆነው ይሰራሉ።
- ከዚህ በተጨማሪ የራሳቸዉ የሆነ የህክምና መገልገያዎችና መድሃኒቶች ማምረቻ ማእከላት የኖሩዋቸዋል።

በአጠቃላይ ልዩ ሆስፒታሎቹ የአለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ደረጃ ያላቸው ሆነዉ ***10ኙ*** አለምአቀፋዊና ***60ኙ*** የአፍሪካን የህክምና ቱሪዝም ገበያን የሚሸፍኑ ይሆናሉ። እነዚህ ተቋማት በግል ባለሃብቶች ትብብር የሚቋቋሙ ሲሆኑ በፌደራል የተቀናጀ የጤና አስተዳደር፣ የጤና ጥበቃ ሚ/ር እና በማህበረሰቡ ልዩ ድጋፍ እና ክትትል ይደረግላቸዋል።

ምዕራፍ ሰባት

የጤናው ዘርፍ የሰዉ ኃይል ልማት

ኢዜማ በጤናዉ ዘርፍ የሰዉ ኃይሉ ልማትን በዕቅድ መምራት ማለት ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል በሁሉም ቦታ ለሰለጠነ በክህሎት ለዳበረና በስነምግባሩ ለታነፀ የሰዉ ኃይል ተደራሽ እንዲሆን ማስቻል አንደሆነ ያምናል፡ ፡ ከዚህ በተጨማሪ በዕቅድ የተመራ የጤና የሰዉ ኃይል የሃገሪቱን የጤና ፖሊሲ፣ ስልቶች (Strategies) እና ዝርዝር የስራ ዕቅዶች እንዲሁም አለም አቀፋዊ ስምምነቶችን (ዘላቂ የልማት ግቦችና (Sustainable Development Goals) ሁሉን ደራሽ የጤና አገልግሎቶች (Universal Access to Health)) ተግባራዊ ለማድረግ ዋነኛ ግብዓት እንደሆነ ኢዜማ በፅኑ ያምናል።

ከላይ የተዘረዘሩትን የሀገር ውስጥና አለምአቀፋዊ ስምምነቶችና ግዴታዎች ጥራታቸውንና ደረጃቸውን ጠብቀው ተግባራዊ እንዲሆኑ አገልግሎቶቹን የሚሰጡት የጤና ሰራተኞች ዓይነት (አስታማሚ ነርሶች፣ ኃላፊ ነርሶች፣ አዋላጅ ነርሶች፣ ዶክተሮች፣ የጤና ኦፊሰሮች፣ ፋርማሲስቶች፣ የየጠየናና ስነምግብ ተመራማሪዎች፣ የመረጃ አስተዳደር ባለሞያዎች፣ የማህበረሰብ ሰራተኞች፣ የላቦራቶሪ ሰራተኞች፣ የማህበረሰብ ጤና ሰራተኞች፣ ወዘተ*.*)፤ ሰራተኞቹ ሊኖራቸዉ የሚገቡ የእውቀትና ክህሎቶች ደረጃዎች፤ የእያንዳንዱ የጤና ሰራተኛ ብዛተ በዝርዝር የሚያሳይ፣ የሰራተኛውን ሁለንተናዊ እድገትና በሀገሪቱ ፍትሃዊ የሆነ ስርጭት እንዲኖር የሚያስችል የጤናዉ ዘርፍ የሰዉ ኃይል ልማት ዕቅድ መሰራት እንዳለበት በፅኑ ያምናል።

7.1 ኢዜማ የሚዘገጀዉ የጤናዉ ዘርፍ የሰዉ ኃይል ልማት ዕቅድ

- ኢዜማ በሁለንተናዊ አቀራረብ ያምናል፤ ይህም ማለት የሰራተኛዉን ክፍያዎች (ደመወዝ፣ ማነቃቂያ ክፍያዎች፣ ወዘተ*.*)፤ ፖሊሲ (ዝርዝር የስራ ኃላፊነቶች፣ የስራ ላይ ደህንነት መመሪያዎች፣ የሰራተኞችን ተጠያቂነትና አስተዳደራዊ ዝምድናዎች)፤ ትምህርት (መሰረታዊ ትምህርትና ተከታታይ ስልጠናዎች)፤ ትብብሮች(ከማህበረሰብ፣ ማህበረሰብ አባላት፣ የግሉ ማህበረሰብ፣ ወዘተ*.* ጋር)፤ የመምራት ብቃት (ለጤናሰራተኞች ኃላፊዎችና የጤና ሰራተኞች ዕቅድን ተግባራዊነት ለሚመሩና ለሚያስተባብሩ ኃላፊዎች፣ ወዘተ*.*) እና የጤናዉ ዘርፍ ሰዉ ኃይል አስተዳደር (የሰዉ ኃይሉን የተመለከተ መረጃ አሰባሰብ አያያዝና አጠቃቀም፣ ድጋፋዊ ክትትልና ዉጤታማነትን ማሳደግ) በምሉዕነት ያካተተ መሆን አለበት ማለት ነው። *(Global Health Workforce Alliance/World Health Organization HRH Action Framework.)*
- ኢዜማ ሁሉን አቀፍ ይሆናል፤ ይህም ሁሉንም የጤናዉ ዘርፍ ሰራተኞች (የጤና አገልግሎት (Clinical) ሰራተኞች፣ የጤና ተንከባካቢዎች (የስነምግብ ባለሞያዎች፣ የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች የስነ

ዓዕምሮ ባለሞያዎች ወዘተ.ይ) እና የምርምር፣ መረጃ አያያዝ፣ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የሚያጠቃልል ይሆናል።

- በኢትዮጵያ ውስጥ የጤና አገልግሎት የሚሰጡትን ተቋማት (የመንግስት ጤና ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የእምነት ድርጅቶች፣ አትራፊ የግል ጤና ተቋማት) አካታች፣ ፍትሃዊና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት ለሁሉም የማህበረሰብ አባላት መስጠታቸውን የሚያረጋግጥ የሆናል። ከዚህ በተጨማሪ የመንግስት ጤና ተቋዋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የእምነት ድርጅቶች፣ አትራፊ የግል ጤና ተቋማት መደጋገፍና መተባበር እንዲኖራቸው መንግስት መመሪያዎችን የማውጣትና የማስተባበር ኃለፊነትን ይወስዳል። አንዲሁም እንደየአስፈላጊነቱ የሃገር በቀል መድሃኒቶች የሚኖራዉን ጠቀሜታና የባህል አዋቂዎችን ስራ እውቅና በመስጠት መሰጠት የሚችሉትን አገልግሎቶች ለማህበረሰቡ እንዲሰጡ ድጋፍ ያደረግላቸዋል።
- የጤናው ዘርፍ የሰዉ ኃይል ልማት ዕቅድ ባጠቃላይ የሀገሪቱ የጤና ስርዓትና የጤና የሰዉ ኃይል ልማት ለሃገራዊ የልማትና የእድገት ሂደት ዉስጥ ተደጋጋፊና ዉጤታማ ድርሻ እንዲኖረው ሆኖ ይቀረፃል፡ ፡ ፍትሃዊና አግላይ ያልሆነ የጤናዉ የሰው ኃይል ስርጭትን ያረጋገጠ ይሆናል። የጤናው የሰው ኃይል ስርጭት የጤና አገልግሎቶችን በቀላሉ መድረስ ለማይችሉ የማህበረሰብ ክፍሎች አገልግሎቶቹን ለማዳረስ በሚያስችል መልኩ መሰራት እንዳለበት ኢዜማ ያምናል። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ለጤና ባለሞያዎች የማነቃቂያ ዘዴዎችን ተግባራዊ በማድረግ፣ መሰረታዊ የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶችንና የማህበረሰብ ጤና ሰራተኞችን (የማህበረሰብ ነርሶችን፣ ለልምምድ መርሃግብር የሚወጡ የጤና ሙያ ተማሪዎች እና መሰረታዊ ጤና ተጠሪዎችን) በማጠናከርና በማስፋፋት፣ የጤና ትምህርት ስርአቱ ፍትሃዊነትን (በተማሪዎች መረጣ ወቅት፣ የነፃ ትምህርት በማመቻቸት ወዘተ.ይ)በሚያጠናክር መልኩ መቅረፅ፣ እንዲሁም የመሰረተ ልማትን በማስፋትና በማጠነከር ለኑሮ አመቺ ሁኔታንና አካባቢን ለመፍጠር ለተቀናጀ የልማት ስራ ከሌሎች የልማት አጋሮች ጋር በትብብር መስራተን ያካተተ እንዲሆን ያደርጋል።
- ፍትሃዊ ከሆነ መልከአ ምድራዊ ስርጭት በተጨማሪ የጤናው ዘርፍ ሰው ኃይል ልማት አቅድ የጤናው ዘርፍ የሰው ኃይል በተለያዩ የጤና ዘርፍ እርከኖች (መሰረታዊ የጤና ማዕከላት፣ ማህበረሰባዊ የጤና ማዕከላት፣ የወረዳ ሆስፒታሎች፣ የፌደራል ሆስፒታሎችና ልዩ ሆስፒታሎች) ውስጥና ጤና ድርጅቶቹ በሚሰጡት የአገልግሎት ዓይነቶች (አጠቃላይና እስፔሺያሊሰት) መሰረት ስርጭታቸዉ ፍትሃዊ እንዲሆን ይሰራል። በአጠቃላይ በማህበረሰባዊና መሰረታዊ የጤና ማዕከላት አጠቃላይ (Generalist) ባለሙያዎች ሲመደቡ በሆስፒታሎች ደግሞ በአብዛኛው እስፔሺያሊሰቶች ይመደባሉ።
- ኢዜማ የጤናው ዘርፍ ሰው ኃይል ልማት አቅድ በማህበረሰቡ ውስጥ የተገለሉና በቁጥር አነስተኛ ለሆኑ የማህበረሰብ አባላት (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አረጋዊያን፣ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች፣ የአካልና ስነአዕምሮ ጉዳተኞችን) ፍላጎቶችንና ምኞታቸዉን ያካተተ ሆኖ እንዲቀረፅ ይደርጋል። የእነዚህ የህብረተሰብ አካላት ፍላጎትና ምኞት ለመድረስ የጤናዉ ዘርፍ ሰው ኃይል ልማት አቅድ አወጣጥ ሂደቱ እነዚህን የማህበረሰብ አባላትንም ያካተተ መሆኑንም ያረጋግጣል፤ የስነ- አእምሮ ጤና ባለሞያዎችን በበቂ ቁጥርና ጥራት ማሰልጠን፤ የጤና ባለሞያዎችን በአካል ጉዳተኞች፣ በኢኮኖሚ ተጎጂ የሆኑ ሰዎች፣ ከHIV/AIDS ጋር የሚኖሩ ሰዎችና በገጠር ኑዋሪዎች (አርሶና አርብቶ አደሮች) መብቶች ዙሪያ በቂ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ኢዜማ ያምናል ።

- ኢዜማ የጤናዉ ዘርፍ ሰዉ ኃይል ልማት አቅድ በአካላዊና በማህበረሰባዊ አወቃቀር ምክንያት የሚመጣን የፆታ ልዩነት (ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ፣ ለሙያዊ እድገት እኩል እድል መስጠት፣ በስራ ቦታ ፆታዊና አካላዊ ጥቃቶችን ማስወገድ) በሚፈታ መልኩ እንዲዘጋጅ ያደርጋል። ጤናማነቱና (Healthy) ደህንነቱ (Security) የሚያስተማምንና አቅርቦቱና መሰረተ ልማቱ የተሙዋላለት የስራ ሁኔታ መፍጠር የጤናው ዘርፍ ሰዉ ኃይል ልማት እቅድ አንድ አካል ሆኖ ይቀረፃል።
- ኢዜማ ሁለንተናዊ ጥንቃቄ (Universal Precaution) እንዲሁም ሌሎች በሽታ የመከላከያና መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ ለጤናው ዘርፍ ሰራተኞች አስፈላጊ የሆኑትን የጤና አገልግሎቶችን ተጠቃሚ በማድረግ፣ በቀላሉ በበሽታ እንዳይያዙና አካላዊ ጉዳት አንዳይደርስባቸው የአካል መከላከያ ዘዴዎችን አንዲጠቀሙ ለማድረግ፣ የስነ አእምሮ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚያስችል የጤናው ዘርፍ ሰው ኃይል ልማት አቅድ እውን ያደርጋል።
- የጤናው ዘርፍ ሰራተኞች የተሰጣቸውን የስራ ሃላፊነት በተቀመጠው መለኪያ መሰረት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችሉ ኢዜማ የሃገሪቱ አጠቃላይ የጤና ፖሊሲና ሰትራቴጂዎች ባስቀመጡት መሰረት የሚያስፈልጉትን የመድሃኒት፣ የህክምና ቁሳቁሶችን፣ የመገልገያ መሳሪያዎችን የተሟላ አቅርቦት እንዲኖራቸውና የጤና ተቋሙ አስፈላጊ የሆኑትን መሰረተ ልማቶችን (የኤሌክትሪክ ሃይልና የንፁህ ውሃ አቅርቦት) እንዲሞላላቸው በሚያስችል መልኩ እንዲቀረፁ ያደርጋል።

7.2 የጤናዉ ዘርፍ የሰዉ ኃይል ማካካሻና ጥቅማጥቅሞች

ኢዜማ የጤናዉ ዘርፍ የሰው ኃይል ህይወቱን ትርጉም ባለው መልክ መምራት የሚያስችል ደመወዝና ጥቅማጥቅሞችን በሚያረጋግጥ መልኩ የጤናው ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት እቅዱን ያዘጋጃል። የጤናዉ ዘርፍ ሰራተኞች ፍልሰትን ለመቀነስ ኢዜማ በጤናው ዘርፍ የሰዉ ኃይል ልማት እቅዱ ውስጥ የገንዘብና ገንዘብ ነክ ያልሆኑ የማትጊያና ማካካሻ ዘዴዎችን (የመኖሪያ ቤት ማቅረብ ወይም ወጭን መጋራት፣ የምሳ ወጭን መሸፈን፣ በብድር አስፈላጊ ቁሳቁሶችን (ምሳሌ፡ መኪና) እንዲገዙ ማስቻል፣ የጨቅላ ህፃናት ማቆያ ማዘጋጀት፣ ለሰሩት መልካም/ሰናይ ስራ እውቅና መስጠት፣ ድጋፋዊ የስራ ክትትል ማድረግ፣ ለጤናማና (Healthy) ደህንነት(Security) ተስማሚ የሆነ የስራ ቦታ ማዘጋጀት በዋናነት እንዲካተቱ ያደርጋል።

7.3 ለጤናዉ ዘርፍ የሰዉ ኃይል ትምህርትና ስልጠና

- የቅድመ-ምረቃም ሆነ ድኅረ-ምረቃ የጤና ትምህርትን በተመለከተ የጤና ሚኒስትር ሃላፊነቶችን ወስዶ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
- የሰው ልጆች ሰብአዊ መብት፣ ግብረገብነትና ስነምግባር ትምህርት፡- በኢዜማ የሚዘጋጀዉ የጤናዉ ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት ዕቅድ በጤና ባለሞያዎች መሰረታዊ ትምህርት/ስልጠና የትምህርት ዝግጅት መመሪያ (Cirricula) ውስጥ የስው ከመደበኛዉ የጤና አገልግሎት ትምህርቶች በተጨማሪ የሰብአዊ መብቶች ትምህርትና ግብረገብነትንና ስነምግባርን እንዲያካትት ሆኖ ይዘጋጃል።
- የጤናው ዘርፍ መሰረታዊ ትምህርት፡- ኢዜማ የጤናው ዘርፍ መሰረታዊ ትምህርት ኢትዮጵያ የገባችውን ሃገራዊና አለምአቀፋዊ ጤና ነክ ግዴታዎችን ለመወጣት የሚያስችላትን የሰው ኃይል በቁጥርና በጥራት ማሟላት በሚችልበት መልኩ የተዘጋጀ እንዲሆን ያደርጋል።
- ተከታታይ ስልጠናዎች፡- የጤናው ዘርፍ የስው ኃይል ልማት ዕቅዱ የጤና ባለሞያዎች የሚያገለግሉትን ማህበረሰብ ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችላቸው ተከታታይ ስልጠናን

በመስራት መማር (Onjob Training)፣ ማህበረሰብን መሰረት ያደርገ ተግባር ተኮር ስልጠና (Hands-On Training)፣ የአዳራሽ ዉስጥ ስልጠና፣ ወዘተ*ኒ*) ያካተተ ሆኖ ይዘጋጃል፡

- በግል ባለሃብቶች የሚመሰረቱትና የጤና አገልግሎት ለመስጠት በተሰማሩት ተቋማት ውስጥ የሚሠማራው የሰው ኃይል የትምህርት ደረጃቸው፣ ለሚመደቡበት የስራ መደብ የሚኖራቸው ልምምድ፣ የሚጠበቅባቸው ግብረገብነትና ስነምግባር በሚመለከተው አካል የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላታቸውንና የሚሰጡዋቸው የጤና አገልግሎቶች ጥራታቸውን የጠበቁና ፍትሀዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመንግስት ድጋፍና ክትትል አስፈላጊ መሆኑን ኢዜማ በፅኑ ያምናል።

7.3 የጤናዉ የሰዉ ኃይል የሙያ ስነምግባርና የህግ ከለላ

- የአንድ ማህበረሰብ የጤንነቱ መሟላት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የኑሮ ሁኔታ መረጋገጥና የጤና አገልግሎቱን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንዲዳረስ ኃላፊነቱን የተሸከመው መንግሰት ተሸሽሎ በሚያወጣው ህገመንግስት፣ በሚከተለው አደረጃጀት፣ ድንጋጌዎች፣ ፖሊሲ፣ የማስፈፀሚያ ስልቶች፣ መመሪያዎችና አቅዶች መሰረት የጤናው የሰው ኃይል በግረገብነት፣ ስነምግባር፣ በህግና ስርአት የታነፀ መሆን አለበት።
- በኢዜማ የሚመሰረተው መንግስት የሚጣልበትን የማህበረሰቡን ጤንነት፣ ደህንነቱንና ፍትሃዊ ስርአት መስፈኑን ለማረጋገጥ ከሚወስዳቸው ውሳኔዎች ውስጥ የማህበረሰቡን ከበሽታዎች መከላከልና መንከባከብ እንዲቻል፣ የጤና ባለሞያዎቹ ደረጃውን የጠበቀና ጥራት ያለው አገልግሎት አንዲሰጡና በግብረገብነትና በስነምግባር የታነፁ አንዲሆኑ የሚያስችል ሀገራዊ የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጭና የስነምግባር ቦርድ አንዲሁም በየጤና ተቋማት ደረጃ የህክምናና ስነምግባር ቦርድ እንዲመሰረቱና ግዴታቸውን እንዲወጡ ያደርጋል።
- ሀገራዊ የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጭና የስነምግባር ቦርድ ተማሪዎች ከተለያየ የጤና ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመረቁ የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ ሊያገኙ የሚሰችላቸውን ዝርዝር መስፈርቶች ያወጣል። ዝርዝር መስፈርቶቹን የሙያ ማህበራት ኃላፊነት በመዉሰድ አዘጋጅተዉ ለቦርዱ በማቅረብ ያፀድቅሉ። በዚህመ መሰረት የሙያ ማኅበራት በተጠናከረ መልኩ እንዲደራጁ ይደረጋል፤ ከመንግስትም ድጋፍ እና ክትትል ያገኛሉ።
- በጤና ተቋማት ደረጃ የህክምናና ስነምግባር ቦርድን በተመለከተ በየደረጃው የሚቋቋሙት ቦርዶች አይነተኛ ተግባራቸው በየእርከኑ ያሉት የጤና ተቋማት ውስጥ የሚሰጡትን የጤና አገልግሎቶች ግልፅ በሆነ መንገድ ዝርዝር ማውጣት ይሆናል።በየደረጃው ከተለያየ አቅጣጫ ለሚቀርቡ የሙያና ስነምግባር ጉድለቶች ማረሚያና መቀጣጫ ሊሆኑ የሚችሉ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ ዝርዝር ደንቦችና መመሪዎችን ያወጣል ተግባራዊም ያደርጋል።
- ከሙያ ፍቃድ እድሳት ጋር የተያያዘ ጉዳይ የየባለሙያ ማህበራቱ ሃላፊነት እና ድርሻ እንዲሆን ማህበራትን ይደግፋል ያበረታታል እንዲሁም ይከታተላል።

ምዕራፍ ስምንት

የመድሃኒት እና የህክምና ግብአት አቅርቦት

የህክምና ግብዓት እና መድሃኒት አቅርቦት ለጤናው ስርአት የጀርባ አጥንት መሆኑ እሙን ነው። የአቅርቦት ስርዓቱ የኢትዮጵያን የጤና ስርአት በአለፉት አመታት በእጅጉ ሲፈታተን እና የህብረተሰቡን እሮሮ ሲያባብስ መቆየቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ውጤታማ ያልሆነ የመድሃኒት እና የህክምና ግብአት አቅርቦት የጤና አጠባበቅ ስርአቱን ከስሩ በመናድ ህብረተሰቡ በጤና ተቋማት ላይ ያለውን እምነት ይሸረሽራል።

የመድሃኒት እና የህክምና ግብዓት አቅርቦት ውጤታማነት የሚለካው የህብት አጠቃቀም፤ ብቁ የሰው ሃይል፤ ዘመን አፈራሽ ቴክኖሎጂ እና መረጃን በመጠቀም ከማምረቻ ቦታ ወደ ተገልጋዩ በአግባቡ ማድረስ ሲቻል ነው። ይህም ራሱን የቻለ ሳይንስ ሆኖ በከፍተኛ ተቋም ደረጃ ብዙ ጥናቶች ይሰራበታል።

8.1 የምግብ፤መድሀኒት እና የህክምና ግብአት ቁጥጥር ባለስልጣን

ይህ አደረጃጀት የጋራ ጤና (shared health governance) አካል ይሆናል። ራሱን በሰው ሃይል እና ቴክኖሎጂ እንዲያጠናክር ከተለያዩ አጋር ድርጁቶች ጋር በትብብር ይሰራል። የመድሃኒት እና ህክምና ግብአት ፋብሪካዎችን ፤ መድሃኒቶች እና የህክምና ግብአት ደህንነት እና ጥራትን ይቆጣጠራል። ጥራት መቆጣጠር የሚችሉ ላቦራቶሪዎችን ያስገነባል። ሃገር አቀፍ መሰረታዊ መድሃኒት ዝረዝሮችን ያዘጋጃል። አዳዲስ መድሀኒቶችም ሆነ የህክምና ግብአቶችን ይመዘግባል ጥቅም ላይ እንዲውሉም ፈቃድ ይሰጣል ያድሳል። ሀገር አቀፍ የምርመራ እና የህክምና መመሪያ (Protocol) እንዲዘጋጅ ያስተባብራል። ሐገራዊ የሆነ ምክንያታዊ የመድሀኒት ፕሮግራሞች ያዘጋጃል። የመጠቀሚያ ግዜያቸው ያለፉ እና አደገኛ ግብአቶች በአግባቡ መወገዳቸውን ይቆጣጠራል።

የመድሃኒት እና ህክምና ግብአት አቅርቦቱን ለማሳለጥ የተለያዩ አደረጃጀቶችን ይዘረጋል እነዚህም በመድሃኒት እና የህክምና መገልገያ እቃዎች ባለስልጣን ስር ትስስር የሚኖራቸው አደረጃጀቶች ይሆናሉ።

1. የህብረተሰብ የመድሃኒት እና የምክምና መገልገያ እቃዎች ኤጀንሲ
2. የግል የመድሃኒት እና የህክምና መገልገያ እቃዎች ኤጀንሲ

8.1.1 የህብረተሰብ የመድሃኒት እና የህክምና መገልገያ እቃዎች ኤጀንሲ

ይህ የህብረተሰብ ኤጀንሲ በዋነኝነት የሚሰራው ስራ ለህብረሰተብ ጤና አገልግሎት የሚያገለግሉ መድሃኒቶች እና የህክምና መገልገያ እቃዎችን በተመለከተ በሃለፊነት መስራት ነው። እነዚህ በእርዳታ በብድር ወይም በግዢ የሚገኙ ሊሆን ይችላል ስለነዚህ አይነት መድሃኒቶችና የመገልገያ መሳሪያዎች ስርጭት እና ፍትሃዊ ክፍፍል ሃላፊነተቱን ወስዶ ይሰራል።

8.1.2 ሃገር አቀፍ የመድሃኒት እና የህክምና መገልገያ እቃዎች ኤጀንሲ

በሃገር አቀፍ ደረጃ ለግሉ ዘርፍም ሆነ ለመንግስት ሆስፒታሎች በየክልሉ በሚኖር የመዋቅር ትስስር ተከትሎ የሚቀርቡ መድሃኒቶችን እና የህክምና መገልገያ እቃዎች የማቅረብ ሀላፊነት ይኖርበታል። በዋነኝነት በግሉ ዘረፍ የሚቋቋም ቢሆንም የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ እና የትርፍ ድርሻ አወሳሰን ላይ

ተመስርቶ የሚቋቋምና የሚሰራ ይሆናል። በሀገር አቀፍ ደረጃ ኤጀንሲዉን በተመለከተ አመራርና የስርጭት አቅጣጫዉን የሚሰጠው የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ቢሆንም የግል ባለሃብቶችን በማበረታት አቅርቦትና ስርጭቱን ግን ኤጀንሲው በሀላፊነት እንዲወስደው ይደረጋል።

ኤጀንሲው ከመድሃኒቶች በተጨማሪ ለሚኖሩት የህክምና መገልገያ እቃዎቹ ጥገናና እንክብካቤ ማድርግ የሚችሉ የባዬ ሜዲካል ኢንጂነሪንግ ባለሙያዎችን በማህበር በማደራጀት በሃገር አቀፍ ደረጃ አገልግሎቱ የሚደርስበትን መንገድ ያመቻቻል፡

8.1.3 የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች አከፋፋይ

በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚኖሩ የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች አከፋፋይ መደብሮች ባለሙያዎችን በማህበር በማደራጀት፣ በማቋቋምና የብድር አቅርቦትነ በማመቻቸት ባለሞያዎች የየራሳቸውን ስራ እንዲፈጥሩ ብሎም የሙያውን ስነምግባር በጠበቀ መልኩ እንዲሰሩ ይደረጋል።

ምዕራፍ ዘጠኝ

የጤና አገልግሎቶች አሰጣጥ

የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት መሰረቱ የሚከተለው ፖሊሲ፤ የማህበረሰቡ የጤና ተሳትፎ፤ የድጋፍና ክትትል ብሎም ቁጥጥር የሚያደርገው ተቋም ጥንካሬ እና ትብብር ላይ መሰረት ያደረገ ድምር ውጤት ነው፡ ፡ ይህ ድምር ውጤት ነው ለማህበረሰቡ የሚደረሰውን የጤና አገልግሎት ተደራሽነት፤ ጥራቱን የጠበቀ መሆን እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነቱን እንዲወስን የሚያደርገው። ሌላው የጤና አገልግሎት ስንል መረሳት የሌለበት ጉዳይ የጤና አገልግሎት ማካተት ያለበትን ዘርፎች ሲሆን እነዚህም ጤና ማጎልበት (ማበልፀግን)፣ በሽታን መከላከል፣ የፈውስ ህክምና፣ የማገገም የጤና አገልግሎት እንዲሁም የማስታገስ የጤና አገልግሎትን ያካተታል።

የጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ለማህበረሰቡ በሚኖራች ቅርበትና አግባብነት ባላቸው መሰረታዊ የማህበረሰቡ አደረጃጀቶች መካከል በሚኖረው ግንኙነት፣ ትስስርና ትብብር ጥንካሬ ነው። ለዚህም ኢዜማ የጤና አገልግሎቱን ተጠቃሚው ማህበረሰብ በቅርብ ርቀት መጠቀም እንዲችል ሀገራዊ፣ ፌደራላዊ፣ ወረዳ፣ ማህበረሰባዊና መሰረታዊ የጤና አገልግሎት እርከኖችና ማእከላትን በየእርከኑ ከማደራጀት በተጨማሪ ማህበራዊና መሰረታዊ የጤና ማዕከላት ከማህበረሰቡ መሰረታዊ አደረጃጀቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት፣ ትስስርና ትብብር በመፍጠር የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቱን ውጤታማ ለማድረግ፣ የፈውስ ጤና አገልግሎቱን ለማህበረሰቡ ለማስተዋወቅ፣ የፈውስ ጤና የአገልግሎቱን ተጠቃሚነት ለማስፋትና ወረርሺኞች መኖራቸዉን በፍጥነት አዉቆ ለመቆጣጠርና የሚያስከትሉትን ጉዳት ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

ኢዜማ በእያንዳንዱ እርከን (ሀገራዊ፣ ፌደራላዊ፣ ወረዳና ማህበረሰባዊ) ለሚደራጁት የጤና ማዕከላት (ልዩ ሆስፒታሎች፣ ሪፈራል ሆስፒታሎች፣ ወረዳ ሆስፒታሎችና ማህበረሰባዊና መሰረታዊ የጤና ማዕከላት) የሚሰጡትን የጤና አገልግሎቶች፣ የሚይዙትን መድሃኒቶችና የህክምና ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር (Package) የማህበረሰቡን የጤና ችግሮች በሚፈታ መልኩና ኢትዮጵያ የገባችውን ሃገራዊና ዓለም አቀፋዊ ግዴታዎችን በሚያሳካ መልኩ ያዘጋጃል።

የጤና አገልግሎቱ ጥራት (ከቀጥተኛና ተጓዳኝ ጉዳቶች ነፃ መሆኑን፣ ውጤታማነታቸውን፣ በቅንጅት መተግበራቸውን፣ ቀጣይነታቸውንና ማህበረሰብ ተኮርነታቸውን) በሚያሰጠብቅ መልኩ የአገልግሎቶችና የአገልግሎቶች አሰጣጥ ደርጃዎች (**መቄሮቃሳሮቄሳቂ**) ፣ ደንቦችና መመሪዎች በየእርከኑ ተዘጋጅተው ስራ ላይ ይውላሉ። እነዚህ ደንቦችና መመሪያዎች የጤና አገልግሎት ሰጪዎቹ ለሚሰጡት የጤና አገልግሎት ጥራት (ከቀጥተኛና ተጓዳኝ ጉዳቶች ነፃ መሆኑን፣ ውጤታማነታቸውን፣ በቅንጅት መተግበራቸውን፣ ቀጣይነታቸውንና ማህበረሰብ ተኮርነታቸውን) ቀጥተኛ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል።

በተለይ በግል ባለሃብቶች የሚደራጁ የህክምና ተቋማትና የሚሰጡት የጤና አገልግሎቶች እና በመንግስት ተቋማት የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች ተመሳሳይ ደረጃ እና ጥራት እንዲኖራቸው ይሰራል፤ ልዩ የሆኑ አስፈላጊ እና አንገብጋቢ ሀክምናዎች በግል ተቋማት የሚሰጡ ሆነው በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ መሆን የሚችሉበትን መንገድ መንግስት ድጋፍና እገዛ በማድረግ በማህበረሰብ ሞር የጤና መድህን አገልግሎቶች እነዲሸፈን በማድረግ ለማህበረሰቡ ያመቻቻል። ኢንሹራንሶች እና ዋስትናዎችን በማበረታታት ከኪስ ቀጥጠኛ ወጪ የሚሆኑ ክፍያዎችን ለመቀነስ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል፣ ቀጥተኛ ክፍያ ጋር በተያያዘ አስፈላጊ የሆነ የጤና አገልግሎት ማህበረሰቡ ማግኘት እንዳይቸገር ስርዓቶችን በመዘርጋት ኢዜማ ሃላፊነቶችን ይወጣል።

9.1 የጤና አገልግሎት አሰጣጥ

የጤና አገልግሎትን አሰጣጥ በተመለከተ ህንፃ ለመስራት የተደረገውን ጥረት ያክል ፣ በሰው ሃይል እና ግብአት ላይ የተሰራው እጅግ ደካማ እና አንዳንዴም አሳፋሪ ነው ። የጤና አገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመን፤ ተደራሽ ለማድረግ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ዜጎች ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ አደረጃጀቱ በተለያየ ሁኔታ ይሆናል።

1. መንግሥታዊ አደረጃጀት (ከዚህ በፊት ተገልጿል)
2. የግሉ ዘርፍ
3. መንግስታዊ ያልሆነ አደረጃጀት (**ሐሀሐ**)

መንግስታዊ አደረጃጀቱ ከማህበረሰብ የጤና አገልግሎት ጀምሮ እስከ ልዩ ሆስፒታል ያለው ሲሆን በምዕራፍ አምስት እና ስድስት የጤና አገልግሎት እና የፈውስ ህክምና በሚለው ክፍል በስፋት ተመልክቷል።

የግሉ ዘርፍ የሚሰጠው አገልግሎት እስከ ወረዳ ባለው አደረጃጀት የመንግስትን መዋቅር ጋር ተመሳሳይ የሚሆን ሲሆን ከክልል ሆስፒታሎች ጀምሮ ያለው አደረጃጃት ግን በጥናት ላይ ተመስርቶ ለዜጎች የተሻለ አገልግሎት መስጠት በሚያስችለው መልኩ የሚደራጅ ይሆናል እስከዚያው ግን አሁን ባለው አደረጃጀት ላይ የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎበት የሚተገበር ይሆናል

መንግስታዊ ያልሆነ (**ሐሀሐ**) አደረጃጀቱ ከግሉ ዘርፍ ጋር የተዛመደ ይሆናል። ለዝቅተኛ የማህበረሰቡን ከፍሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል። ከላይ የተገለጹት ሁሉም አደረጃጀቶች ሃገራዊ ዝቅተኛ መሟላት ያለበት ደረጃ (**ቋቄሮቃሳሮቄሳ**) ይወጣላቸዋል። አገልግሎት አሰጣጡም በመመሪያ እና ደንብ እንዲደገፍ ይደረጋል።

ምዕራፍ አስር

የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት

የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ትርጉም ያለው በጥራቱ፣ በወቅታዊነቱና በተቀባይነቱ አስተማማኝ የሆነ መረጃ ትክክለኛ፣ ወቅታዊና ችግር ፈቺ የሆኑ ውሳኔዎችን ለመስጠት መሰረት እንደሆነና ጤናማ፣ አምራችና ብቁ የሆነ ማህበረሰብን ለመገንባት ጠዋት ማታ ለሚተጋ ዜጋ ገሃድ የወጣ ሃቅ ነዉ። ኢዜማ አስተማማኝ የሆነ የመረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት፣ የመቀመርና ትርጉም መስጠት፣ የስርጭትና አጠቃቀም ስርአትን ዘመኑ በፈቀደው ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ የመረጃ አስተዳደር ስርአት በየአሰተዳደራዊ እርከኖቹ በመላው አገሪቱ መዘርጋት የጤና ፖሊሲን ለመንደፍና ተግባራዊ ለማድረግ፣ የጤናውን አስተዳደርና ክትትል ዉጤታማ ለማድረግ፣ የጥናትና ምርምር ዘርፉን ለማጎልበት፣ የጤና ሰው ኃይሉን ለማጎልበት፣ የጤና ትምህርቱንና ስልጠናዉን ዉጤታማ ለማድረግ፣ ለጤናዉ ዘርፍ የሚሆን ሃብት ለማሰባሰብ፣ የጤና አገልግሎቱን ውጤታማ ለማድረግና ጤናማ ማህበረሰብን ለመፍጠር ለሚደረግ ርብርብ የማዕዘን ድንጋይ እንደሆነ በፅኑ ያምናል።

ኢዜማ የሚነድፈውና በተግባር የሚከተለው የመረጃ አስተዳደር ስርዓት በጤናው ዘርፍ በሚወሰዱ የውሳኔ ሂደቶች ውስጥ መረጃን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በመቀመር፣ ትርጉም በመስጠት፣ በማሰራጨት፣ ጠቀሜታ ላይ በማዋልና ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ የሚያስችል ደረጃ በደረጃ ወደተግባርና ወደተፈላጊው ግብ የሚያደርስ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል።

ይህም በመሆኑ የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓቱ የሚያፈልቃቸውን መረጃዎች ለሚመለከታቸውና ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ማሰራጨትና ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ተገቢ መሆኑ ይታመናል።

10.1 የጤና መረጃ ማሰባሰቢያ ዕርከኖች

የጤናዉ መረጃ አስተዳደር ስርአቱ የታለመለትን ግብ እንዲመታና በየአስተዳደራዊ እርከኖቹ የታሰበውን ተግባር እንዲከውን መረጃዎች የሚሰባሰቡት በሚከተሉት እርከኖች ይሆናል፡-

- **በግለሰብ ደረጃ፡-** ወደ ጤና ተቋማቱ ለህክምና ከሚመጡ ታካሚዎች የግል ማህደሮች ላይ የግል ማንነት መገለጫዎች፣ የተደረገላቸዉ የምርመራ አይነቶች፣ ተለይቶ የታወቀ የጤና ችግር፣ ያገኙት የጤና አገልግሎቶችና ህክምናዎች ለውሳኔ በሚረዳ መልኩ ማስፈርና መጠቀም ይቻላል።
- **በጤና ተቋማት ደረጃ ፡-** በጤና ተቋማቱ ዉስጥ ካለው የታካሚዎች የግል ማህደሮች የተሰበሰበውን መረጃዎች፣ የመድሃኒት አስተዳደር መረጃዎች፣ የላቦራቶሪ መረጃዎች፣ የኤክስራይ ክፍል መረጃዎችና ሌሎች አስተዳደራዊ መረጃዎች ባንድ ላይ በማቀናበር ለጤና አስተዳደር የስራ መሪዎች ለጤና ተቋማቱ የሚያስፈልገውን የሃብት መጠን ለመገመት፣ የመድሃኒትና ሌሎች ቁሳቁስ የግዢ ስርአትን ለመቀመር፣ የማህበረሰብ ጤና አግልግሎትን ዕቅድ ለማውጣት በሚረዳቸው መልኩ ይዘጋጃሉ። ከዚህ በተጨማሪ በጤና ተቋማት ደረጃ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ለጤና ተቋማቱ ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ ለፖሊሲ ቀማሪዎችና የስራ ስልት አውጪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ኢዜማ በፅኑ ያምናል።
- **በማህበረሰብ ደረጃ ፡-** የጤና ተቋማት በሚሰጠው የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ከሆኑና ተጠቃሚ ካልሆኑ የማህበረሰብ አባላት የሚሰበሰበው ጤና ነክ መረጃዎች በዋናነት የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት ይዘትና አሰጣጥ ላይ ለሚወሰዱ ውሳኔዎች በዋና ግብአትነት ያገለግላሉ። በጤና ተቋማቱ የሚሰበሰበው መረጃ ጥራቱና ወካይነቱ አስተማማኝ በማይሆንበት ጊዜና በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን እምነቶች፣

አመለካከትና ድርጊቶች ለማጥናት ሲፈለግ የቤት ለቤት የጥናት ዳሰሳ በዋናነት በማህበረሰብ ደረጃ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ በመሆን ያገለግላል።

የማህበረሰብ ጤና ዳሰሳ ጥናት በጤና ተቁዋማትና በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰበሰቡትን መረጃዎች በማጣመር በአካባቢዉ ያሉትን ጤና ነክ ችግሮች ለቅሞ በማውጣት ለችግሮቹ ውጤታማ መፍትሄዎች በማፈላለግ ረገድ አይነተኛ ሚና ይጫወታል። የዚህ አይነቱ ክንውን በዋናነት አስፈላጊ የሚሆነው በሽታዎች በወረርሺኝ መልክ በሚከሰቱበት ጊዜ ነዉ። በዚህ ሂደት ውስጥ የመረጃዎቹና የሚወሰዱት አርምጃዎች/ክንውኖች በሽታን በመከላከልና በመቆጣጠር ኃላፊነት ላለባቸው ኃላፊዎች ለማድረስ ወቅታዊ ማድረግ የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓቱ ኃላፊነት የሆናል።

10.2 የጤና መረጃዎች አስተዳደር ሥልቶች

የማህበረሰብ አደረጃጀቶች (የሴቶች ፣ እናቶችና ሕፃናት)፣ የወጣቶች፣ የአዛውንቶች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ወዘተ) በተናጥልም ሆነ በጋራ (በማህበረሰብ መር የጤና ዋስትና አደረጃጀታቸዉ) ያሉባቸውን ጤና ነክ ችግሮች ነቅሶ በማውጣት፣ ለችግሮቻቸው መፍትሄ ብለው ያስቀመጡዋቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች፣ የጤና ችግር ሲያጋጥማቸው አገልግሎት የሚያገኙባቸው የጤና ተቁዋማትንና ተቁዋማቱ የሚሰጡዋቸውን የጤና አገልሎቶች፣ ለሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች ተጠቃሚ አባላት፣ ባገኙት የጤና አገልግሎት ለችግሮቻቸው መፍትሄ ያገኙ የማህበረሰብ አባላት፣ ወዘተ*ያ*የመሳሰሉትን መረጃዎች መልክ ባለው ረገድ ሚያደራጁበት የመረጃ ቋት መዝገብ አዲኖራቸው ያደረጋል። ከመረጃ ቋታቸዉ በመቀነስ ስምምነት በተደረሰበት የጊዜ እርከን (በሳምነት፣ በወር፣ በሦሥት ወር፣ ወዘተ*ያ*) ለዚሁ አላማ የሚዘጋጁ መረጃ ማስተላለፊያ ቅፆችን በመሙላት በመሰረታዊ አስተዳደራቸው ውስጥ ለሚገኘው መሰረታዊ የጤና ማዕከል በአስተባባሪዎቻቸው አማካኝነት ገቢ ያደርጋሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ስምምነት በተደረሰበት የጊዜ እርከን (በሳምነት፣ በወር፣ በሦሥት ወር፣ ወዘተ*ያ*) በሚደረገዉ ቋሚ የማህበሰብ አደረጃጀቶች ተወካዮችና በመሰረታዊ ጤና ማዕከል ሰራተኞች መካከል በሚደረገው ማህበረሰባዊ ውይይት (Community Dialogue) ወቅት ከሚሰጣቸው ተከታታይ ጤና ነክ ስልጠና በተጨማሪ በችግሮቻቸው ላይ ተወያይተው ውሳኔ ይወስናሉ፣ ለውሳኔያቸው ማስፈፀሚያ ዕቅድ ያወጣሉ፣ ይተገብራሉ፣ አፈፃፀማቸውንም የከታተላሉ፣ ሪፖርት ያደርጋሉ።

በመሰረታዊ ጤና ማዕከል ደረጃ የጤና መረጃዎችን ለማደራጀት በሙያው የሰለጠነና በሃላፊነት የተመደበው ባለሙያ የመሰረታዊ ጤና ማዕከሉ የሰራቸውን ዝርዝር ሥራዎች፣ ከማህበረሰቡ አደረጃጀቶች የተሰበሰቡትን ዝርዝር የስራ ክንውኖችና በማህበሰባዊ ውይይት ወቅት የተደረሱ ውሳኔዎችና ክንውኖችን ከማህበረሰብ ጤና ማእከል የመረጃ ቋት ጋር ተወራራሽነት ባለው መልኩ በኤሌክትሮኒክስ ታብሌት በተዘጋጀ የመረጃ ቋት በማደራጀትና በሁሉም ፌደሬሽኖችና በሃገር ደረጃ በተመረጠ የመረጃ አሰተዳደር ቴክኖሎጂ (ኮምፒውተር ፕሮግራም) አማካኝነት ወደ የቀጥታ አስተዳደራዊ ግንኙነት ወዳላቸው ማህበረሰባዊ የጤና ማዕከል በየወሩ ገቢ ያደርጋሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ስምምነት በተደረሰበት የጊዜ እርከን (በሳምነት፣ በወር፣ በሦሥት ወር፣ ወዘተ*ያ*) በሚደረገው ቋሚ በጤና ሰራተኞች መካከል በሚደረገዉ የውይይት መድረክ ወቅት ከሚሰጣቸው ተከታታይ ሙያዊ ስልጠና በተጨማሪ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ ተወያተው ውሳኔ ይወስናሉ፣ ለውሳኔያቸዉ ማስፈፀሚያ ዕቅድ ያወጣሉ፣ ይተገብራሉ፣ ለአፈፃፀማቸውም ክትትል ያደርጋሉ።

በማህበረሰብ ጤና ማዕከል ደርጃ የጤና መረጃዎችን ለማደራጀት በሙያው የሰለጠነና በሃላፊነት የተመደበው ባለሙያ የማህበረሰብ ጤና ማዕከሉ የሰራቸውን ዝርዝር ሥራዎች፣ ከመሰረታዊ ጤና ማዕከል የተሰበሰቡትን ዝርዝር የስራ ክንውኖች ከወረዳ ሆስፒታሎች የመረጃ ቋት ጋር ተወራራሽነት ባለው መልኩ በሁሉም ክልሎችና በሃገር ደረጃ በተመረጠ የመረጃ አሰተዳደር ቴክኖሎጂ (ኮምፒውተር ፕሮግራም) አማካኝነት ወደ የቀጥታ አስተዳደራዊ ግንኙነት ወዳላቸው ወረዳ ሆሰፒታል በየወሩ ገቢ ያደርጋሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ስምምነት በተደረሰበት የጊዜ እርከን (በሳምነት፣ በወር፣ በሦሥት ወር፣ ወዘተ.) በሚደረገው የሆስፒታሎችና ማህበረሰብ ጤና ማዕከል ጤና ሰራተኞች መካከል በሚደረገው የውይይት መድረክ ወቅት ከሚሰጣቸው ተከታታይ ሙያዊ ስልጠና በተጨማሪ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ ተወያይተው ውሳኔ ይወስናሉ፣ ለውሳኔያቸው ማስፈፀሚያ ዕቅድ ያወጣሉ፣ ይተገብራሉ፣ አፈፃፀማቸውንም ክትትል ያደርጋሉ።

በወረዳ ሆስፒታል ደረጃ የጤና መረጃዎችን ለማደራጀት በሙያው የሰለጠነና በሃላፊነት የተመደበው ባለሙያ ሆሰፒታሉ የሰራቸውን ዝርዝር ሥራዎች፣ ከማህበረሰባዊ ጤና ማዕከል የተሰበሰቡትን ዝርዝር የስራ ክንውኖች ከፌደራል ሆስፒታሎች የመረጃ ቋት ጋር ተወራራሽነት ባለው መልኩ በሁሉም ፌደሬሽኖችና በሃገር ደረጃ በተመረጠ የመረጃ አሰተዳደር ቴክኖሎጂ (ኮምፒውተር ፕሮግራም) አማካኝነት ወደ የቀጥታ አስተዳደራዊ ግንኙነት ወዳላቸዉ የፌደራል ሆሰፒታል በየወሩ ገቢ የደርጋሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ስምምነት በተደረሰበት የጊዜ እርከን (በሳምነት፣ በወር፣ በሦሥት ወር፣ ወዘተ.) በሚደረገው የፌደራልና ወረዳ ሆሰፒታሎች ጤና ሰራተኞች መካከል በሚደረገው የውይይት መድረክ ወቅት ከሚሰጣቸው ተከታታይ ሙያዊ ስልጠና በተጨማሪ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ ተወያይተው ውሳኔ ይወስናሉ፣ ለውሳኔያቸው ማስፈፀሚያ ዕቅድ ያወጣሉ፣ ይተገብራሉ፣ አፈፃፀማቸውንም ክትትል ያደርጋሉ።

በፌደራል ሆስፒታል ደርጃ የጤና መረጃዎችን ለማደራጀት በሙያው የሰለጠነና በሃላፊነት የተመደበው ባለሙያ ፌደራል ሆሰፒታሉ የሰራቸውን ዝርዝር ሥራዎች፣ ከወረዳ ሆስፒታል የተሰበሰቡትን ዝርዝር የስራ ክንውኖች ከሀገራዊ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የመረጃ ቋት ጋር ተወራራሽነት ባለው መልኩ በሁሉም ፌደሬሽኖችና በሃገር ደረጃ በተመረጠ የመረጃ አሰተዳደር ቴክኖሎጂ (ኮምፒውተር ፕሮግራም) አማካኝነት ወደ ሀገራዊ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየወሩ ገቢ ያደርጋሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ስምምነት በተደረሰበት የጊዜ እርከን (በሳምነት፣ በወር፣ በሦሥት ወር፣ ወዘተ.) በሚደረገው የሀገራዊ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ፌደራል ሆሰፒታሎች ጤና ሰራተኞች መካከል በሚደረገው የውይይት መድረክ ወቅት ከሚሰጣቸው ተከታታይ ሙያዊ ስልጠና በተጨማሪ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ ተወያይተው ውሳኔ ይወስናሉ፣ ለውሳኔያቸው ማስፈፀሚያ ዕቅድ ያወጣሉ፣ ይተገብራሉ፣ አፈፃፀማቸውንም ክትትል ያደርጋሉ።

በልዩ ሆስፒታል ደርጃ የጤና መረጃዎችን ለማደራጀት በሙያው የሰለጠነና በሃላፊነት የተመደበው ባለሙያ ልዩ ሆሰፒታሉ የሰራቸውን ዝርዝር ሥራዎች ከሀገራዊ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የመረጃ ቋት ጋር ተወራራሽነት ባለው መልኩ በሁሉም ፌደሬሽኖችና በሃገር ደረጃ በተመረጠ የመረጃ አሰተዳደር ቴክኖሎጂ (ኮምፒውተር ፕሮግራም) አማካኝነት ወደ ሀገራዊ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየወሩ ገቢ ያደርጋሉ።

በግል ባለሀብቶች እንዲሁም ባለሙያዎች የሚቋቋሙ የጤና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከላይ በተዘረዘረው የመረጃ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን እንደ ዕርከናቸው ልክ የመረጃ አስተዳደር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ወቅታዊና ታማኝነቱን ያልለቀቀ መረጃ የማድረስ ግዴታ ይኖርባቸዋል።

ምዕራፍ አስራ አንድ

የጤና አገልግሎት የሃብት ምንጭና አስተዳደር

በኢዜማ የጤና ፖሊሲ መሰረት የሚሰጡት የጤና አገልግሎቶች የማህበረሰብ ጤና እና የፈውስ ሰጪ ጤና አገልግሎቶች በመባል በሁለት ክፍሎች ይከፈላል። የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች ጥቅል ማህበረሰባዊ ጠቀሜታን (Health Services with Public Good) እና ለግለሰብም ለማህበረሰብም ጠቀሜታ ያላችዉ (Merit-Good) የጤና አገልግሎቶችን የሚያጠቃልል ይሆናል።

ጥቅል ማህበረሰባዊ ጠቀሜታን (Health Services with Public Good) የሚያረጋግጡ የጤና አገልግሎቶች በሽታን አምጪና አስተላላፊ ነፍሳት (Vectors) ቁጥጥር፣ የንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ የግልና የጋራ ንፅህና አጠባበቅ፣ የአካባቢና የተፈጥሮ ሚዛናዊነት ጥበቃ፣ በጤናው ዘርፍ ጥልቅ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ የጤና አገልግሎቶችን ማስተዋወቅና የጤና ትምህርቶች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤

ለግለሰብም ለማህበረሰብም ጠቀሜታ ያቸላዉ (Merit-Good) የጤና አገልግሎቶች ደግሞ የተለያዩ የክትባት አገልግሎቶች፣ በከፍተኛ ደረጃ ተላላፊ (Contagious Diseases) በሽታዎችን (የሳንባ በሽታ (Tuberculosis)፤ በግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች (Sexually Transmitted Diseases (STD) HIVን ጨምሮ) ፤ በአልኮልና አነቃቂዎች ሱሰኝነት፤ የህፃናትን ጤና አገልግሎቶች (የትምህርት ቤቶች ጤና አገልግሎቶች፣ የመተንፈሻ አካል መታወክ፣ ተቅማጥ፣ ኩፍኝ፣ ወባ፣ ባጭር ጊዜ የሚከሰት የምግብ እጥረት ወዘተ)፤ የእናቶች የጤና አገልግሎቶች (የስነምግብ አገልግሎት፣ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት፣ ቅድመ-ወሊድ ምርመራ፣ በሰለጠነ ባለሞያ የወሊድ አገልግሎት መስጠት፣ ድህረ-ወሊድ ክትትል) የሚያጠቃልሉ ይሆናሉ።

የፈውስ ጤና አገልግሎቶች ደግሞ ያለምንም ማስጠንቀቂያ የሚከሰቱ ህመሞች፣ ድንገተኛ የሆኑ በሽታዎች፣ በአዝጋሚነት የሚከሰቱና ተጠባቂ የጤና መታዎከችና፣ በአኗኗር ዘይቤ/ ልምድ ምክንያት የሚከሰቱ የጤና መታወከችን መፍትሄ የሚሰጥ አገልግሎት ነው።

11.1 የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት

የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች በዋናነት ጥቅል ማህበረሰባዊ ጠቀሜታን (Health Services with Public Good) የሚያረጋግጡ የጤና አገልግሎቶች እና ለግለሰብም ለማህበረሰብም ጠቀሜታ ያላችዉ (Merit-Good) የጤና አገልግሎቶች የሚያጠቃልል ሆኖ በመሰረታዊ የጤና ማዕከላት፣ በማህበረሰብ የጤና ማዕከላትና በወረዳ ሆስፒታሎች የሚሰጡ ይሆናሉ።

የፈውስ ጤና አገልግሎቶች ፡ -

- ያለምንም ማስጠንቀቂያ የሚከሰቱ ህመሞች (ድንገተኛ የሆኑ በሽታዎች)፣
- በአዝጋሚነት የሚከሰቱና ተጠባቂ የጤና መታወከችና፣
- በአኗኗር ዘይቤ/ ልምድ ምክንያት የሚከሰቱ የጤና መታወከችን መፍትሄ የሚሰጥ ይሆናል

በዋናነት በማህበረሰብ የጤና ማዕከላት፣ በወረዳ ሆሰፒታሎች፣ በፌደራል ሆሰፒታሎችና በሃገራዊ ልዩ ሆስፒታሎች ይሰጣሉ።

11.2 የጤናዉ ዘርፍ የሃብት ምንጮች ጠቀሜታዎች

ለጤናው ዘርፍ በተለያዩ መንገዶች በቂና አስተማማኝ የሃብት ምንጭ መኖሩ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል :-

- ማህበረሰባዊና የፈዉስ የጤና አገልግሎት ፕሮግራሞች በአግባቡ መኖራቸውን (Availability and accessibility) ያረጋግጣል ፣
- መልክአ ምድራዊ ተደራሽነታቸውን ፍትሃዊ (quitable) ለማድረግ፣ ጥራታቸው ደረጃውን የጠበቀና አስተማማኝ ያደርጋል
- በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች (በሴቶችና ወንዶች፣ በሃብታምና ድሃዎች፣ በገጠርና ከተሞች፣ በአርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች፣ በአካል ጉዳተኞች፣ ወጣቶች፣ አረጋዊያን፣ ወዘተ.) መካከል ያለውን ኢ-ፍትሃዊ የሆነውን የጤና አገልግሎቶች ስርጭት ያስተካክላል።
- የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርአቱን በአደረጃጀት፣ በሰው ኃይል፣ በቴክኖሎጂ፣ በመድሃኒቶች የተሟላ በማድረግ እንዲሁም ከማህበረሰቡ ጋር የሚኖረውን ትስስር፣ መተባበርና መረዳዳትን በማጠናከርና ውጤታማ በማድረግ የሰዎችን የጤና ሁኔታ ከማሻሻሉ በተጨማሪ የማህበረሰቡን ማህበረሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ደህንነቶች ያረጋግጣል።
- ከሁሉም በላይ የማህበረሰብ ጤናማ መሆን ለአለም አቀፋዊ ምርታማነት በ9% አስተዋፅዖ ከማድረጉ በተጨማሪ ከፍተኛ ለሆነ የማህበረሰብ ክፍል የሥራ ዕድል ይፈጥራል።
- እነዚህን ዘርፈ - ብዙ የሆኑ የጤና አገልግሎቶችን ጠቀሜታዎች ለማህበረሰቡ ለማረጋገጥ ኢዜማ መንግስታዊና ግላዊ የሃብት ምንጮችን በዋናነትና በአግባቡ ጠቀሜታ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡ :
- መንግስታዊ የሆኑ የሃብት ምንጮች ከማህበረሰቡ የሚሰበሰቡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብሮች (Tax)፣ ከማህበረሰቡ የሚሰበሰቡ የአገልግሎት ክፍያዎች (Users Charge)፣ እንደየሁኔታው ማህበራዊ ግዴታዎች (Mandates) በመተግበር፣ ከተለያዩ ሀገራት የሚደረግ የልማት ድጋፎች (Grants)፣ ብድሮችና (Loans) የበጎ አድራጎት አስተዋፅዎች (Charity Contributions) ዋና ዋናዎቹ ናቸው።
- ግላዊ የሃብት ምንጮች (Private Revenue) ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች የአገልግሎት ቀጥታ ከፍያ (Out-of-Pockete)፣ ዜጋ መር የጤና ዋስትና (Community Led Health Insurance)፣ ከባለሀብቶች ወይም አለምአቀፋዊ ድርጅቶች የሚገኝ ድጋፍ (Grants)፣ ብድሮች (Loans) እና በጎአድራጎት ድጋፎች (Charitable Contributions) በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

11.3 የጤናው ዘርፍ የሃብት ምንጮች

ከተለያዩ መንግስታዊና ግላዊ የጤናው ዘርፍ የሃብት ምንጮች የሚሰበሰበው ሃብት አግባብነት ባለው የጋራ ቋቶች ውስጥ በመሆን በትክክለኛውና አግባብነት ባለው መልኩ መተዳደር ይኖርበታል። በዚህም መሰረት:-

11.3.1 በመንግስታዊ ሃብት የጤና አገልግሎቶች አቅርቦት (Accessibility)

የግለሰብንም ሆን የማህበረሰብን ጤንነት መጠበቅ የሰው ልጆች ካሏቸዉ ስብዓዊ መብቶች አንዱ በመሆኑ ሁሉም የማህበረሰብ አባል ለጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት ሊኖረው እንደሚገባ ኢዜማ ጠንቅቆ ይረዳል። በመሆኑም የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች በመሰረታዊ ጤና ማዕከላት፣ በማህበረሰብ ጤና ማዕከላትና

በወረዳ ሆስፒታሎች አማካኝነት በመንግስታዊ ተቋማት ኃላፊነት ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል። የተቋማት ግንባታ፣ አስፈላጊ የሆኑ የሰው ኃይል ምደባ፣ የምርመራ (Diagnostic) መሳሪያዎችና ኬሚካሎች፣ የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦቶች እና ሌሎች ወጪዎች በመንግስታዊ የበጀት ምንጮች የሚሸፈን ይሆናል።

አንዲሁም የፈውስ ጤና አገልግሎቶች በወረዳ ሆስፒታሎች፣ በፌደራል ሆስፒታሎች እና ሀገራዊ ልዩ ሆስፒታሎች አማካኝነት በመንግስታዊ ተቋማትና በጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር ኃላፊነት ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል። የተቋማት ግንባታ፣ አስፈላጊ የሆኑ የሰው ኃይል ምደባ፣ የምርመራ (Diagnostic) መሳሪያዎችና ኬሚካሎች፣ የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦቶች እና ሌሎች ወጪዎች በመንግስታዊ የበጀት ምንጮች የሚሸፈን ይሆናል።

11.3.2 በግል ባለሃብቶች የጤና አገልግሎቶች አቅርቦት (Accessibility)

ከዚህ በተጨማሪ ኢዜማ የማህበረሰብ ጤናን ለማረጋገጥ መንግስትና የመንግስት ተቋማት ብቻቸውን ሊወጡት እንደማይችሉ በሚገባ ይረዳል። በዚህም መሰረት ለግል ባለሃብቱ አመቺ የሆኑ ፖሊሲዎችና የአሰራር ስልቶችን በመንደፍ ባለሃብቱ የፈውስ ጤና አገልግሎቶች በወረዳ ሆስፒታሎች፣ በፌደራል ሆስፒታሎች እና በሃገራዊ ልዩ ሆስፒታሎች ትይዩ በግሉ ማህበረሰብ በሚመሰረቱ የጤና ተቋማት አማካኝነት ተደራሽ እንዲያደርጉ ይደረጋል። የግል የጤና ተቋማት ግንባታ፣ አስፈላጊ የሆኑ የሰው ኃይል ምደባ፣ የምርመራ (Diagnostic) መሳሪያዎችና ኬሚካሎች፣ የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦቶች እና ሌሎች ወጪዎች በግል ተቋማትና በባለሃብቶች የበጀት ምንጮች የሚሸፈን ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ በመንግስት የጤና ተቋማት ውስጥ መለስተኛ ቀዶ ህክምና አገልግሎቶች፣ ከፍተኛ ቴክኖሎጂዎችን የሚያስፈልጉ የምርመራ (Diagnostic) መሳሪያዎችና ኬሚካሎች፣ የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦቶችን ለግል ተቋማትና ባለሃብቶች በከፊል በማዞር አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል። በዚህም መሰረት በመንግስት ተቁዋማት ውስጥ የግል ባለሃብቱ በጤና አገልግሎቶች አቅርቦትና ጥራትን ለማስጠበቅ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ኢዜማ ይረዳል።

11.3.3 ለጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት (Service Use) የሃብት ምንጭ

የማህበረሰቡ የጤና አገልግሎቶችን የመጠቀም ፍላጎትና ተጠቃሚነት በከፍተኛ ደረጃ መጨመር፣ የጤና አገልግሎቶችን በአግባቡ አለመጠቀም፣ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚታገዙ ህክምናዎች ዋጋ ከፍተኛ መሆን፣ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ከሚፈልጉት የረጅም ጊዜ ህክምናና ከሚፈጥሩዋቸዉ ተጉዋዳኝና አጣዳፊ ህመሞች ምክንያት የህከምና ዋጋቸዉ የማይቀመስ መሆኑ፣ መንግስት ለጤናዉ የሚመድበው በጀት አናሳ መሆኑና ያለችውን አነስተኛ በጀት በአግባቡ የመጠቀም ልምምዱ ባለመኖሩ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ለሚያገኙት አገልግሎት ቀጥታ በመክፈል (Out-of-Pocket) በወጪ ማካካስ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ አገልግሎት መስጠት የግድ ይላል።

የወጪ ማካካስ ላይ የተመሰረተ አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም ሰዎች የጤና አገልግሎት በሚያስፈልጋቸው ወቅት ለህክምና አገልግሎት የሚውል ክፍያ የመክፈል አቅሙ ሊኖራቸው ይገባል። የህክምና አገልግሎቱ ዋጋ ከፍተኛ መሆኑና በአጠቃላይ የቤተሰብ የሃብት ገቢና ወጪ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ሰዎች ለህክምና አገልግሎት የሚውል ጥሬ ገንዘብ በእጃቸዉ ላይኖር ይችላል። በዚህ ምክንት ሰዎች ለሚፈልጉት የጤና አገልግሎት የሚያስፈልጋቸዉን ከፍተኛ ወጪ ከመንግስትና ከማህበረሰቡ ጋር የሚጋሩበት ስልትና የአሰራር ዘዴ መፍጠር እንደሚያስፈልግ ኢዜማ ጠንቅቆ ይረዳል።

ኢዜማ ሰዎች ለሚፈልጉት የጤና አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ከፍተኛ ወጪ ከመንግስትና ከማህበረሰቡ ጋር የሚጋሩበት ስልትና የአሰራር ዘዴ እውን ለማድረግ መንግስት፣ ዜጋ መር የጤና ዋስትና አትራፊ የጤና ዋሰትና ተቁዋማት ተጠናክረው ወደስራ አንዲገቡና ኃላፊነት እንዲወስዱ ያደርጋል።

11.4 መንግስታዊ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ክፍያ ሽፋን

በመሰረታዊ የጤና ማዕከላት፣ በማህበረሰብ የጤና ማዕከላትና በወረዳ ሆስፒታሎች የሚሰጡትን ጥራታቸውን የጠበቁ የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ለማቅረብና አገልግሎቱን በአግባቡ ለመስጠት ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚጠበቀውን ክፍያ ሙሉ በሙሉ ከመንግስት በሚመደብ ባጀት የሚሸፈን ይሆናል።

የግል የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ክፍያ ሽፋን

የአገልግሎት ክፍያ (User-Charge/Out-of-Pocket)

በየትኛውም የጤና ዋስትና ያልታቀፉ ዜጎች ከመንግስት ጤና ተቁዋማት የጤና አገልግሎቶችን ለማግኘት ሲፈልጉ የጤና ተቁዋማቱን ወጪዎች ለመሸፈን አላማ ያደረገ የገልግሎት ክፍያ (user-Charge) በቀጥታ ይፈፅማሉ። የጤና አገልግሎቱን የሚያገኙት ከግልና ትርፍ ላይ ከተመሰረተ የጤና ተቁዋም ከሆነ ትርፉንም የማከለ የገልግሎት ክፍያ (Out-of-Pocket) በቀጥታ ይከፍላሉ።

11.4.1 የዜጎች መር የጤና ዋስትና

ዜጎች በህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ህይወታቸውን የሚነካና እነሱን የሚመለከቱ ጉዳየችን በተመለከተ በቀጥታ መሳተፍ በተፈጥሮ ያገኙት ሰብአዊ መብታቸው እንደሆነ ኢዜማ ጠንቅቆ ይረዳል። በዚህም መሰረት ዜጎች ማግኘት የሚገባቸውን የጤና አገልግሎቶች ጥራትና ተደራሽነት ለማረጋገጥ በባለቤትነት ቀጥተኛ ተሳትፎና ሂደቱ በራሳቸው መመራት እንዳለበት ኢዜማ በፅኑ ያምናል። ከዚህ መሰረታዊ እምነት በመነሳት ዜጎች ከመሰረታዊ የአስተዳደር እርከን በመጀመር፤ በእረሻ፣ በእንስሳ እርባታ፣ በመንግታዊም ሆነ በግል የስራ ቦታዎች የሚተዳደሩ ዜጎች እስከ ሀገር አቀፋዊ አስተዳደር እርከን ድረስ አደረጃጀት በመፍጠር፤ የጋራ የሆነ ለጤና አገልግሎት የሚውል የሃብት ክምችት (Pool) በመፍጠር፤ ሊታከም በሚችል በሽታ መሰቃየትና ህክምና ለማግኘት በሚያስፈልግ ከፍተኛ ክፍያ ምክንያት የሚፈጠርን ግለሰብአዊና ማህበረሰባዊ ጫና በመጋራት፤ የጋራ ችግርን በጋራ ለመቅረፍ የተቀናጀ አመራር በመፍጠርና ዜጎች የራሳቸውን ችግር በእራሳቸው ጥረት እነዲፈቱ ማስቻል የኢዜማ የጤና ፖሊሲ መሰረታዊ አላማው ነው።

አባል ለመሆንና ግዴታቸውን ተወጥተው ተጠቃሚ ለመሆን ፍላጎት ያላቸው ዜጎች በመሰረታዊ አስተዳደር እርከን፤ በእረሻ፣ በእንስሳ እርባታ፣ በመንግታዊም ሆነ በግል የስራ ቦታዎች የሚተዳደሩ ዜጎች በመሰባሰብ መሰረታዊ ዜጎች መር የጤና ዋስትና ይመሰርታሉ። በመሰረታዊ የአስተዳደር አርከኖች በእረሻ፣ በእንስሳ እርባታ፣ በመንግታዊም ሆነ በግል የስራ ቦታዎች የሚተዳደሩ ዜጎች የሚቁዋቁዋሙት መሰረታዊ ዜጎች መር የጤና ዋስትና አባላት የጤና ዋሰትናውን መሰረታዊ አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣ አባልነት ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚያስተባብርና አባላት ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅሞች በአግባቡ እንዲያገኙ ለአባላቱ ድምፅ ሊሆን የሚችል አመራር ይኖረዋል። ከሁሉም መሰረታዊ አስተዳደር እርከኖችና ከሚመሰረቱት የዜጎች መር የጤና ዋስትናዎች የተመረጡ ተወካዮች በወረዳ አስተዳደር እርከን ደረጃ በተመሳሳይ አደረጃጀት የወረዳ ዜጎች መር የጤና ዋስትናን ይመሰርታሉ። በዚሁ መንገድ ከሁሉም ወረዳ ዜጎች መር የጤና ዋስትናዎች የተመረጡ የማህበረሰቡና የሰራተኞች ተወካዮች በፌደራል አስተዳደር እርከን ደረጃ የፌደራል ዜጎች መር የጤና ዋስትና

አደረጃጀትን ይመሰርታሉ። በመጨረሻም የሁሉም ፌደራላዊ ዜጎች መር የጤና ዋስትና በማህበረሰቡና የሰራተኞች ተወካዮች በጋራ ሃገራዊ ዜጎች መር የጤና ዋስትና ይመሰርታሉ። ከመሰረታዊ ጀምሮ እስከ ሃገራዊ የአስተዳደር እርከኖች የተቋቋሙት ዜጎች መር የጤና ዋሰትና አደረጃጀቶች ህጋዊ ዋስትና እንዲኖራቸው የህግ ማዕቀፎች ይዘጋጅላቸዋል። በየደረጃውም ባለሞያዎችና በዘርፉ እውቀትና ልምምዱ ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጡበትን መንገድ ለማረጋገጥ ኢዜማ አደረጃጀቶቹን ያበቃል።

የሚመሰረተው የዜጎች መር የጤና ዋስትና የሚከተሉት መሰረታዊ ባህሪያት ይኖሩታል ፦

- ዜጎች/ አባ/እማወራዎች በነፍስ ወከፍ በጋራ በተስማሙበት መሰረት በሚኖር አመታዊ መዋጮ በጋራ በማሰባሰብ የጋራ የጤና ችግሮቻቸውን የጋራቸው ጉዳይ ለማድረግ በራሳቸው አመራር የሚፈጥሩት የጤና ዋስትና ነው።
- አባላት የሚከፍሉት ክፍያ ሁሉም አባላት የተስማሙበት እኩል ክፍያ ይሆናል። ይህ ክፍያ ግለሰቦች ከሚገጥማቸው የበሽታ ዓይነት ጋር ምንም ግንኙነት አይኖረውም።
- ከዜጎች መር የጤና ዋስትና አገልግሎት የሚያገኙት በፈቃደኝነት የተመዘገቡና የሚጠበቅባቸውን መዋጮ አጠናቀው ለከፈሉ አባላት ብቻ ነው።
- አባላት የዜጎች መር የጤና ዋስትና አደረጃጀት አባል ሆነው የሚመዘገቡት በፈቃደኝነት ነው።
- የዜጎች መር የጤና ዋስትና ለትርፍ የተመሰረተ አደረጃጀት አይሆንም

ከነዚህ በተጨማሪ ከተለያዩ መንግሰታት፣ ድርጅቶች፣ ባለሀብቶች ወዘተ.. በሚኖሩ ድጋፎች፣ ብድሮችና የበጎ አድራጎት ድጋፎች የሚገኙ ሃብቶች (የገንዘብ፣ የሰዉ ኃይልና ቁሳቁስ) በመንግስትም ሆነ በግል ባለሃብቶች አማካኝነት በሚደረግ ፍትሃዊ ድልድል መሰረት በአግባቡ ለጤና አገልግሎቱ የሚውሉበትን መንገድ ኢዜማ ያመቻቻል።